አዲስ ዘመን

ኢኘድ

ሐሙስ

84ኛ ዓመት ቁጥር 023 መስከረም 23 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ማሻሻያው የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ከማሻሻል አኳያ ምን አስገኘ ?

መስከረም ሰይፉ

ኢትዮጵያ በቅርቡ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ማድረጓ ይታወሳል፡፡ ይህ ማሻሻያ የውጭ ምንዛሬ ተመን በገበያ እንዲመራ ያደረገ ሲሆን ይህም ባንኮች ያዋጣኛል በሚሉት ከደንበኞቻቸው ተደራድረው የውጭ ገንዘቦችን እንዲገዙና እንዲሸጡ እድል ሰጥቷል፡፡ ይህ ፖሊሲ ከባንኮች በተጨማሪም የምንዛሪ ቢሮዎች የውጭ ምንዛሬ ተደራድረው እንዲገዙ በር ከፍቷል፡፡

ከማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያ በኋላ አስመጪዎች ምን ያህል የውጭ ምንዛሬ እያገኙ ነው? የባንኮችስ የውጭ ምንዛሬ ክምች ምን ያህል ነው ? ሲል የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስመጪዎችንና ባንኮችን አነጋግሯል፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው ስማቸውን መግለጽ

ማሻሻያው ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

የኢሬቻ በዓል በረከቶች

ሳሙኤል ወንደሰን

ዜና ሀተታ

በአባ ገዳዎችና ሃደ ሲንቄዎች ግንባር ቀደምነት «መሬ..ሆ» በተሰኘው ዜማ በሚታጀበው የኢሬቻ በዓል ታዳሚያን ባህላዊ አልባሳት፣ ጌጣጌጦች እና ቁሳቁሶች ይዘው ደምቀውና ተውበው የሚታዩበት በዓል ነው። በአሁኑ ወቅት በክብረ በዓሉ ዋዜማ ላይ የኦሮሞ ባህላዊ ጭፈራዎች እና መሰል ባህላዊ ትዕይንቶች በተለያዩ አካባቢዎች በደማቅ ሥነ ሥርዓት እየቀረቡ ነው፡፡ በዓሉን አስመልክቶ የተዘጋጀ ባዛር እና ኤግዚቢሽንም በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል በይፋ ተከፍቷል።

በባዛር እና ኤግዚቢሽኑ የተለያዩ ባህላዊ አልባሳትን ሲሸጡ ያገኘናቸው ወይዘሮ ፋጡማ ሁሴን፤ በመጪው ቅዳሜና እሁድ ለሚከበረው የኢሬቻ በዓል ማድመቂያ የሚሆኑ ባህላዊ አልባሳትን በተሻለ ጥራት ማቅረባቸውን

የኢሬቻ በዓል ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ተኪ ምርቶች የሚያስገኟቸው ሀገራዊ ጥቅሞች

ፋንታነሽ ክንዴ

ኢትዮጵያ በየዓመቱ ለገቢ ምርቶች 18 ቢሊዮን ዶላር የሚደርስ ወጪ እንደምታወጣ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከወጪ ንግድ የምታገኘው ገቢ ግን ከአራት ቢሊዮን ዶላር የዘለለ አይደለም፡፡ ይህም የሀገሪቱ የንግድ ሚዛን የተዛባ እንዲሆን አድርጓል ይላሉ የዘርፉ ምሁራን፡፡

የኢንዱስትሪ ዘርፉን ለማጠናከር እና ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያላትን ጥገኝነት ለመቀነስ ኢትዮጵያ የተኪ ምርት ስትራቴጂ ቀርፃ ተግባራዊ እያደረገች ትገኛለች። በዚህም በ2016 በጀት ዓመት 2 ነጥብ 8 ቢሊዮን ዶላር የሚያወጡ ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት መቻሉን ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ለመሆኑ ተኪ ምርቶችን ማምረት ለዘላቂ ኢኮኖሚ እድገት ያለው አስተዋጽኦ ምንድነው? የሀገሪቱን ተኪ ምርት ለማሳደግስ ምን መሠራት አለበት? በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያ ላይ የምሁራንን አስተያየት ጠይቀናል፡፡

በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህር ሙህዲን ሙሐሙድሁሴን እንደሚሉት፤ የአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ዋና ልኬት የሚባለው የምርት እድገት ነው፡፡

የሀገሪቱ የምርት ሂደት፣ ሥርዓት እና ምርትና ምርታማነት እየጨመረ ሲሄድ የኢኮኖሚ እድገት እያሳየች መሆኑን አመላካች ነው፡፡ የአንድ ሀገር ምርት አድጓል ስንል ገቢዋ ጨምሯል ማለት መሆኑን የሚጠቅሱት ባለሙያው፤ ይህም አዳዲስ የሥራ እድል እንዲፈጠር፣ የዜጎች ፍላጎት የሚያሟሉ ሸቀጦችና አገልግሎቶችን ማቅረብ ያስችላል፡፡

ተኪ ምርቶች ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

የኢሬቻ በዓል የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል

ማርቆስ በሳይ

አዲስ አበባ፡- የኢሬቻ በዓል የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ለማጠናከርና የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማስፋፋት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ፡፡

የከተማው ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሳው (ዶ/ር) ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፤ የኢሬቻ በዓል የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ለማጠናከርና የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማስፋፋት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ኢትዮጵያ የአደባባይ በዓላት ከብዝሃ ባህልና ከህብረ ብሔራዊነት የተገኙ ናቸው ያሉት ኃላፊዋ፤ በዓላቱ ኢትዮጵያውያን በአንድነትና በህብረት ተሳስበው እንዲኖሩ ያደረጉ ምሰሶዎች ናቸው ብለዋል፡፡

በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ በድምቀት የሚከበረው የኢሬቻ በዓልም ከኢትዮጵያ የአደባባይ ክብረ በዓላት መካከል አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዓሉ ህብረትን፣ አንድነት፣ መደጋገፍን እና አብሮነትን የሚያጠናክር ከመሆኑም ባሻገር የፍቅር እሴቶች የሚሰበኩበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ኢሬቻ ካለፈው ዘመን ወደ አዲሱ፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን መሸጋገርን በማሰብ ለፈጣሪ ምስጋና

ሂሩት ካሳው (ዶ/ር)

ሚኤሳ ኤሌማ (ዶ/ር)

የሚቀርብበት የአደባባይ በዓል መሆኑን የገለጹት ሂሩት (ዶ/ር)፤ ኢሬቻ በተለያየ አልባሳትና ጌጣጌጥ አሸብርቆ የሚከበር በመሆኑ ለጥበብ ውጤቶች ፈጠራና ሽያጭ አስተዋጽኦው የጎላ ነው ብለዋል፡፡

በዓሉ በከተማዋ በርካታ ተሳታፊዎች በተገኙበት የሚከበር በመሆኑ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር እንደሚረዳ ጠቅሰው፤ ኢሬቻ ለአዲስ አበባ ትልቅ በረከት ያለው በዓል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ከተማዋን የቱሪስት መሸጋገሪያ ብቻ ሳይሆን መዳረሻ ለማድረግ የሚያስችሉ የቱሪስት መስህብ ያለባት መሆኑዋን ጠቅሰው፤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ጨምሮ የከተማ ልማትም ለቱሪዝም ዘርፉ ምቹ ሁኔታን መፍጠሩን አስረድተዋል፡፡

ኢሬቻና መሰል የአደባባይ በዓላት ደግሞ የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው በመግለጽ፤ በተለይም የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ባህልን ለመፍጠር ትልቅ መሠረት እንዳለው ጠቁመዋል።

በሀገር ውስጥ የማይዳሰስ ቅርስ ሆኖ የተመዘገበው የኢሬቻ በዓል በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገብ እየተሠራ መሆኑንም ኃላፊዋ ገልፀዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ጽህፈት ቤት ፕሬስ ሴክሬታሪያት ኃላፊ ሚኤሳ ኤሌማ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ኢሬቻ ሰው ከሰው እንዲሁም ከተፈጥሮ ጋር ሰላምን የሚያሰፍንበትና ስለ ሰላም የሚሰበክበት በዓል ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል አዲስ አበባ ከተማ በኮሪደር ልማትና መልሶ ማልማት ሥራዎች አምራና ደምቃ ባለችበት የሚከበር በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል ያሉት ኃላፊው፤ በከተማዋ አምስቱም መግቢያ በሮች እንግዶችን ለመቀበል ዝግጅት ተጠናቋል ብለዋል።

ለበዓሉ በከተማ ደረጃ የተለያዩ ዝግጅቶች መደረጋቸውን ጠቅሰው፤ የኢሬቻ ኤግዚቢሽን፣ ፎረምን ጨምሮ በዓሉ እሴቱን ጠብቆ በድምቀት እንዲከበር አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል፡፡

የ2017 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል “ኢሬቻ ለባህላችን ህዳሴ” በሚል መሪ ሃሳብ መስከረም 25 በሆራ ፊንፊኔ እና 26 በሆራ አርሰዲ እንደሚከበር መገለጹ ይታወሳል።

ኮሎኔል ጌትነት አዳነ

መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር)

የሕግ ማስከበር ዘመቻው የክልሉ ሰላም እስኪረጋገጥ ይቀጥላል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል እየተካሄደ ያለው የሕግ የማስከበር ሂደት የሚቆመው የክልሉ ሰላም ሙሉ በሙሉ ሲረጋገጥ መሆኑን የሀገር መከላከያ ሠራዊት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ኮሎኔል ጌትነት አዳነ ገለጹ፡፡

የሕግ ማስከበር ርምጃውን በሚመለከት የሀገር መከላከያ ሠራዊት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ኮሎኔል ጌትነት አዳነ እና የአማራ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር) በጋራ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

ኮሎኔል ጌትነት አዳነ በመግለጫው እንዳሉት፤ በክልሉ የተፈጠረውን የሰላም እጦት ለማስተካከል ሕግ የማስከበር ርምጃ እየተወሰደ ነው። የኦፕሬሽኑ ዓላማ ሁከትን እና ብጥብጥን አስወግዶ ለክልሉ መንግሥት እና ሕዝብ ሰላምን ማስፈን ነው፡፡ ሕግ የማስከበር ሂደቱ የሚቆመው የክልሉ ሰላም ሙሉ በሙሉ ሲረጋገጥ ነው።

በክልሉ ያለው የጽንፈኛ ቡድን የመከላከያን የቆየ ቁስል እየነካ እና ትዕግስቱን እየተፈታተነ የመጣ እንደነበር የጠቀሱት፤ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ኮሎኔል ጌትነት አዳነ ለሕዝብ ሰላም ሲባል ብዙውን ነገር በዝምታ አልፏል። ለመከላከያ ሠራዊት የሚሰጠው ዝቅ ያለ ግምት፣ ስም ማጥፋት እና ማጠልሸት ከአማራ ሕዝብ ሥነ ልቦና የመነጨ እንዳልሆነ ሠራዊቱ ያውቃል ብለዋል፡፡

ሠራዊቱ ለሕዝብ ሰላም ሲባል ዛሬም ከኢትዮጵያዊነቱ ሳይወርድ ሕግ እንደመኪያስከብር ጠቁመው፤ መከላከያ ሠራዊት በጽንፈኛ ቡድኑ ላይ የሚወስደው ኦፕሬሽን የተጠና፣ አውድን የለየ፣ ጀሌን ከመሪ የነጠለ እና የቡድኑን ሴል በሚበጣጥስ መልክ የሚመራ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ከሰሞኑ በከተሞች አካባቢ የተፈጸሙት ርምጃዎች ውጤት ያሳዩ ነበሩ። መከላከያ የአማራን ሕዝብ ስለሚያከብር የክልሉ መንግሥት የጀመረው የሰላም ጥረት ዳር እንዲደርስ የሚችለውን ሁሉ አድርጓል። ከመንግሥት ጋር በሰላማዊ መንገድ የሚነጋገሩ ካሉ በሮቹ ያልተዘጉ ቢሆኑም መከላከያ ግን ሕግ ማስከበሩን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል፡፡

ወታደራዊ ኦፕሬሽኑ በሚገባ የተጠና ነው ያሉት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው፤ ንጹሐንን ለመጠበቅ ሲባል በጥንቃቄ ይመራል። የማኅበራዊ ሚዲያው ጩኸት የሚጠበቅ ነው፡ ፡ በምንም መንገድ ቢሆን ግን መንገድ ዝጉ እና ተማሪዎች አይማሩም ከሚል ጽንፈኛ ቡድን ጋር ከዚህ ያለፈ ትዕግስት አይኖርም ብለዋል።

የአማራ ክልሉ መንግሥት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ መከላከያ እና የክልሉ መንግሥት ሕግ የማስከበሩን ተግባር በቅንጅት እየሠሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የክልሉ መንግሥት የተፈጠረውን ግጭት በሰላማዊ መንገድ ለመቋጨት ተደጋጋሚ የሰላም ጥረቶችን አድርጓል ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ የሰላም በሮችን ሙሉ በሙሉ በመዝጋት ክልሉ ለከፋ ሠብዓዊ እና ቁሳዊ ውድመት ተዳርጓል ነው ያሉት።

መንግሥት ሰፊ የሰላም አማራጮችን ዘርግቶ ችግሮችን በውይይት እና በምክክር ለመፍታት ቢሞክርም ምላሹ ግን በሚፈለገው መንገድ እንዳልሆነ ጠቁመው፤ መንግሥት ሳይወድ በግድ ሕግ ለማስከበር እና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ተገዷል። መከላከያ እና የክልሉ መንግሥት ሕግ የማስከበሩን ተግባር በቅንጅት እየሠሩ ነው ብለዋል።

የክልሉን ሰላም ለማረጋገጥ እና ግጭቱን ለመቋጨት በርካታ መንግሥታዊ እና ሕዝባዊ ውይይቶች እና ምክክሮች ተካሂደው እንደነበር አስታውሰው፤ የታጠቁ ሃይሎች ምላሽ ግን የሕዝብን ስቃይ እና መከራ አባብሷል።

ይባስ ብሎ የታጠቁት ኃይሎች ከሀገሪቷ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር በጋራ እንደሚሠሩ ሳያፍሩ እና ሳይሸማቀቁ አስታውቀዋል ያሉት መንገሻ (ዶ/ር)፤ ጥምረታቸውም በመታዘዝ፣ በሎጀስቲክስ እና በወታደር ድጋፍ እንደተጀመረ መንግሥት ደርሶበታል። ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሕግ የማስከበር እርምጃ ይወስዳል።

ልሂቃን፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና የክልሉ ሕዝብ ከመንግሥት ጎን መቆም እንዳለባቸውም አሳስበው፤ ችግሩ በዘላቂነት እንዲፈታ ሁሉም የድርሻውን መወጣት እንዳለበትም አመላክተዋል፡፡

ሁለንተናዊ የጤና ሽፋንን ለማረጋገጥ የአጋር አካላት ቀጣይነት ያለው ትብብር አስፈላጊ ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ የጤና ሽፋንን ለማረጋገጥ የአጋር አካላት ቀጣይነት ያለው ትብብር አስፈላጊ መሆኑን የጤና ሚኒስቴር ገለጸ። በኢትዮጵያ ላለፉት ስድስት ዓመታት ተግባራዊ ሲደረግ የቆየው የዩናይትድ ስቴትስ የርዳታ ድርጅት «ዩኤስ ኤይድ» የጤና ፋይናንስ ማሻሻያ ፕሮግራም ማጠቃለያ መርሃ ግብር ትናንት ተካሂዷል።

የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር አየለ ተሾመ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ የጤና ፋይናንስ ሥርዓቷን በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ እመርታ ብታሳይም ለሁሉም ዜጎች ፍትሃዊ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አኳያ ተግዳሮቶች አሁንም ቀጥለዋል።

በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ የጤና ሽፋንን ለማረጋገጥ የአጋር አካላት ቀጣይነት ያለው ትብብር አስፈላጊ ነው ያሉት ዶክተር አየለ ፤ ሁለንተናዊ የጤና ሽፋን ግብን ለማሳካት በርካታ ሥራዎችን ይፈልጋል። ሁሉም ዜጎች ፍትሃዊ የሆነ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ የጤና ፋይናንስ ሥርዓት ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል። አሁንም በተደራሽነት እና በጥራት ላይ ክፍተቶች መኖራቸውንም አንስተዋል።

እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት መንግሥት በሀገር ውስጥ ሀብት ማሰባሰብ፣ የውጭ ሀብት አያያዝ፣ ስትራቴጂካዊ ግዥ እና አጠቃላይ የኢንሹራንስ ሥርዓት መዘርጋት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው ያሉት ዶክተር አየለ ተሾመ፤ ሆኖም ሁለንተናዊ የጤና ሽፋን ግብን ለማሳካት ከለጋሾች እና ፈጻሚ አጋሮች ጋር ቀጣይነት ያለው ትብብር እንደሚያስፈልግ አጽንኦት ሰጥተዋል።

ኢትዮጵያ ወደ ጤናማ እና ፍትሃዊ የጤና ፋይናንስ ሥርዓት ጉዞዋን ስታጠናክር ከፊታችን ያሉ ፈተናዎች አዳዲስ መፍትሄዎችን ይሻሉ ሲሉም ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የዩናይትድ ስቴትስ የርዳታ ድርጅት «ዩኤስ ኤይድ» ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኤሌኖር ታንፒንኮ በበኩላቸው፤ የ«ዩኤስ ኤይድ» የጤና ፋይናንስ ማሻሻያ ፕሮግራም በኢትዮጵያ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን አሳድጓል ብለዋል።

የ«ዩኤስ ኤይድ» የጤና ፋይናንስ ማሻሻያ ፕሮግራም በኢትዮጵያ በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁን ገልጸው፤ ፕሮግራሙ የጤና አጠባበቅ ተደራሽነትን በከፍተኛ ደረጃ በማስፋት በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን

ኤሌኖር ታንፒንኮ

ዶክተር አየለ ተሾመ

የፋይናንስ ጫናዎችን መቀነስ ችሏል ነው ያሉት።

በአሁኑ ጊዜ ከ52 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ተጠቃሚ መሆናቸውን ያነሱት ኤሌኖር ታንፒኺ፤ በፕሮግራሙ የሕዝብ ጤና አስተዳደርን ከማጠናከር ባለፈ ለጤና ተቋማት ተጨማሪ የቁሳቁስ እና የተለያዩ ድጋፎች መደረጉን ተናግረዋል።

ፕሮግራሙ በኢትዮጵያ የጤና ፋይናንስ ሥርዓት ላይ ጉልህ መሻሻል ቢያደርግም በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን እና በሌሎች ፕሮግራሞችን የሚታዩ ተግዳሮቶች መኖራቸውን አንስተው፤ «ዩኤስ ኤይድ» እነዚህን ችግሮች ለመፍታት እና የጤና አጠባበቅ ፋይናንስን የበለጠ ለማሻሻል ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ያለውን ሥራ ለመቀጠል ቁርጠኛ መሆኑን ተናግረዋል።

ዜና

የማህበረሰቡን ጤና የታደገው አማራጭ ሃይል

ታደሠ ብናልፈው

አቶ ብርሃኑ ወልዱ

አቶ ጥላሁን ሽመልስ

አቶ ተክተል ማቲዮስ

በኢትዮጵያ የገጠር እናቶች የቤተሰባቸውን የዕለት ጉርስ ለማብሰል፤ ምሽቱን ለማድመቅ የማገዶና የእንስሳት ቅሬት አካልን ይጠቀማሉ፡፡ ማገዶንና የእንስሳት ቅሬት አካላትን ለምግብ ማብሰያነትና የተለያዩ የቤት ውስጥ ሥራዎች ለመሥራት በባህላዊ ምድጃ መጠቀማቸውም ለበሽታ ተላልፈው እንዲሰጡ፤ ጊዜና ጉልበታቸው አላግባብ እንዲባክን እያደረገ ነው፡፡ ህፃናት በጭስ ምክንያት ለጤና ችግር እንዲወድቁ፤ ሴቶችና ልጃገረዶች ማገዶ ለቀማ ሲወጡ ለፆታዊ ጥቃት እንዲጋለጡ አድርጓቸዋል፡፡

መንግሥት የገጠሩ ማህበረሰብ ለጤናና ለኢኮኖሚ ጉዳት፤ ልጃገረዶችን ለፆታዊ ጥቃት የሚያጋልጠውን፤ ሀገርንም ለከፍተኛ ሃይል ብክነት የሚዳርገውን ባህላዊ ምድጃን በተሻሻለ ንጹህ የማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ በመተካት በጤና፤ በኢኮኖሚ ትልቅ ውጤት እያስመዘገበ ነው፡፡

የገጠር ማህበረሰብ ጤንነት ለመጠበቅና የሃይል ብክነትን ለመቆጣጠር ሃይል ቆጣቢና ንፁህ የማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂን ተደራሽ የማድረግ ሥራ በትኩረት እየተሠራ ነው፡፡ በተሠራውም ሥራ 20 ነጥብ አምስት ሚሊዮን የተሻሻሉ የማብሰያ ቴክኖሎጂዎች ተሠራጭተዋል፡፡

የማህበረሰቡን ፍትሐዊ የኢነርጂ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ኤሌክትሪክ፤ የሶላር፤ የባዮማስ ሃይልን የማልማት፤ የተሻሻሉ ንፁህ ምድጃዎችን ተደራሽ የማድረግ፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ የመስጠት ሥራ እየተሰራ ነው፡፡ እየተሠራ ያለውም ሥራ በነጋ በጠባ የቤተሰባቸውን የዕለት ጉርስ ለማብሰል ጉልበታቸውን፣ ጊዜያቸውን አለፍ ሲልም ጤናቸውን የሚነሳቸውን ባህላዊ ምድጃ በዘመናዊ ምድጃ የመተካት፤ ጤናማ ሕይወት እንዲመሩ የማድረግ ተግባር እየተከናወነ ነው፡፡

የገጠር እናቶች ጤናማ ሕይወት እንዲኖሩ ንፁህ የማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽ የማድረግ፤ አነስተኛ ወንዞችን ለሃይል ምንጭነት የመገንባት ሥራ እየተሠራ ነው፤ እንደ እኤአ እስከ 2030 አንድ መቶ 50 ወንዞችን ገንብቶ ለአገልግሎት ለማዋል፤ 30 ነጥብ አምስት ሚሊዮን የተሻሻሉ ንፁህ የማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ለማሰራጨት ሰፊ ክንውን እየተደረገ ነው፡፡

በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር ሥራ አስፈፃሚ ብርሃኑ ወልዱ ለኢፕድ በሰጡት አስተያየት፤ የገጠሩን ማህበረሰብ የንፁህ የማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ያለው ሥራ፤ እናቶች በጭስ ምክንያት የሚደርስባቸውን የጤና ችግር በመቅረፍ ጤናማ ሕይወት እንዲኖሩ እያስቻለ ነው፡፡

ማህበረሰቡ እየተጠቀመባቸው ያሉ የማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች ከፍተኛ ሃይልን የሚያባክኑ ናቸው፤ የሃይል ብክነትን ለመከላከል የተሻሻሉ ዘመናዊ ምድጃዎችን ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው፤ የተሠራውም ሥራ የማህበረሰቡን ጤና ለመጠበቅ የሚያስችል ነው ብለዋል።

ማገዶንና የእንስሳት ቅሬትን በባህላዊ ምድጃ መጠቀም የጤና ችግር ያደርሳል፤ ለማገዶ ፍጆታ የሚውል እንጨት ለመልቀም ጫካ የሚሄዱ ልጃገዶችንም ለፆታዊ ጥቃት ያጋልጣል፤ ህፃናትን ለበሽታ ይዳርጋል፤ማህበረሰቡን ከተለያዩ ችግሮች ተጋላጭነት ለመታደግ የተሻሻሉ ንፁህ ማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

እየተሠራ ባለውም ሥራ 20 ነጥብ አምስት ሚሊዮን የተሻሻሉ የንፁህ የማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን የማሰራጨት ሥራ ተሠርቷል፤ እንደ እኤአ እስከ 2030 31 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዘመናዊ ምድጃዎችን ለማሠራጨት፤ አንድ መቶ 50 አነስተኛ ወንዞችን ለሃይል ማመንጫነት ለመገንባት ታቅዶ እየተሠራ ነው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

የተሻሻሉ የንፁህ ምግብ ማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂን ለገጠሩ ማህበረሰብ ተደራሽ ማድረግ የእናቶችን ጤንነት ከመጠበቅ ባለፈ በቤት ውስጥ ሥራ 70 በመቶ የሚባክነውን ኢነርጂ ለማስቀረት ያስችላል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

የገጠሩን ማህበረሰብ የኢነርጂ ተጠቃሚነቱን ለማሳደግ እንዲቻል የሶላር ስርጭትን ያለበትን ከባቢ ዲጂታል መተግበሪያ ተግባራዊ እየተደረገ ነው፤ መተግበሪያው ተግባራዊ መደረጉ የሶላር ኢነርጂ ስርጭትን ለማሳደግ ይጠቅማል ይላሉ፡፡

የተሻሻሉ ንፁህ የማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ባለመጠቀም ብዙ ሃይል በቤት ውስጥ ይባክናል፤ የሚባክነው ኢነርጂ ለብዙ ፋብሪካዎች ማስተናገድ የሚችል ነው፤ የሃይል ብክነትን ለመከላከል ሃይል ቆጣቢ ምድጃዎችን የማበልፀግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የገጠሩ ማህበረሰብ የኢነርጂ እኩል ተጠቃሚነት ለማስፈን እየተሠራ ባለ ሥራ በ2016 ዓ.ም 14 የሶላር ሚኒግሪዶች ተገንብተዋል፤ በ2017 በጀት ዓመትም ሁለት ሚሊዮን የተሻሻሉ ንጹህ ምድጃዎችን ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ ነው ሲሉ ይጠቁማሉ፡፡

የተበታተኑና ከሃይል ማመንጫ መስመሮች ርቀው የሚኖሩ የገጠር ማህበረሰቦችን የኢነርጂ ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ አነስተኛ ወንዞችን የመገንባት ሥራ እየተሠራ ነው፤ በ2016 ዓ.ም ሶስት አነስተኛ ወንዞችን ለሃይል ማመጫነት የመገንባት ሥራ ተጀምሯል፤ ከተጀመሩት ሶስት የአነስተኛ ወንዞች የሃይል ማመንጫ ግንባታ ውስጥ አንዱ ተጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት እንዲሆን ዝግጅት እየተደረገ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የአማራ ክልል የውሃና ኢነርጂ ቢሮ ምክትል ሃላፊ ጥላሁን ሽመልስ በበኩላቸው፤ የተሻሻሉ ንፁህ የማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች ለገጠሩ ማህበረሰብ ተደራሽ በማድረግ በኩል እየተሠራ ያለው ሥራ ዜጎችን በጤናና በኢኮኖሚ ተጠቃሚነት እያደረገ ነው፡፡

የገጠሩ ማህበረሰብ የንፁህ ማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ማድረግ የእናቶችና የህፃናትን ጤንነት ለመጠበቅ፤ ሴቶችን ከፆታዊ ጥቃት ለማዳን፤ የሀገርን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ትልቅ አበርክቶ አለው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ማህበረሰቡ የንፁህ ማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ መሆኑ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ያስችላል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ለገጠሩ ማህበረሰብ ምን አይነት ቴክኖሎጂ እንደሚያስፈልገው ስትራቴጂ በመንደፍ አስፈላጊውን ቴክኖሎጂ የማልማትና የማሠራጨት ሥራ እየተሠራ ነው፤ እየተሠራ ያለውም ሥራ የሃይል ብክነትን ይከላከላል፤ እናቶች ጤናማ ሕይወት እንዲኖሩ ያስችላል፤ ልጅ ገርዶችን ከፆታዊ ጥቃት ለመጠበቅ ያግዛል ሲሉ ያብራራሉ፡፡

እየተሰራጨ ያለው የንፁህ ማብሰያ ቴክኖሎጂ ከማህበረሰቡ ፍላጎት አንፃር ሲታይ በቂ አይደለም፤ በቂ ለማድረግ በሙያው የሠለጠነ የሰው ሃይል በብዛት ማሠማራትና ትልቅ የገንዘብ አቅም ይጠይቃል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በገጠር የሚኖረው 90 በመቶ ማህበረሰብ የባዮማስ ኢነርጂ ተጠቃሚ ነው፤ የባዮማስ ሃይልን ለመቆጠብ ማህበረሰቡ የተሻሻሉ ንፁህ የማብሰያ ምድጃዎችን እንዲጠቀም እየተደረገ ነው፤ ይህም በጤናው ላይ የሚደርሰውን ችግር እየቀረፈለት ነው ሲሉ በማከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ የአማራጭ ኢነርጂ ልማትና ሽግግር ዳይሬክተር ተከተል ማቲዮስ ይገልጻሉ፡፡

የተሻሻሉ ንፁህ የማብሰያ ምድጃ ቴክኖሎጂዎችን ለገጠሩ ማህበረሰብ ተደራሽ ማድረግ ደንን ከምንጣሮ፤ እናቶችና ህፃናትን ከጤና ሁከት ለመታደግ ትልቅ ጠቀሜታ አለው፤ እስካሁን የተሠራውም ሥራ ትልቅ ውጤት አሳይቷል ብለዋል፡፡

የገጠሩ ማህበረሰብ በማገዶ ጭስ ለተለያዩ የጤና ችግሮች ይጋለጣል፤ ማህበረሰቡን የማገዶ ጭስ በጤናው ላይ የሚያደርሰውን ችግር በመከላከል ጤናማ ሕይወት እንዲመራ ለማድረግ ሃይል ቆጣቢና የተሻሻሉ ንፁህ የማብሰያ የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ተበታትኖ የሚኖረውን ማህበረሰብ ፍትሕዊ የኢነርጂ ተጠቃሚ ለማድረግ በፌዴራልም ሆነ በክልል በጀት ተይዞ አነስተኛ ወንዞችን ለሃይል ማመንጫነት የመገንባት ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

የሕዝቡን አቅም በመጠቀም ጥያቄዎች እንደሚመለሱ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ገለጸ

ሔርሞን ፍቃዱ

አቶ ጌታቸው ረዳ

አዲስ አበባ፡- የሕዝቡ የተደራጀ አቅም በመጠቀም ጥያቄዎችን በአጭር ጊዜ ለመመለስ እንደሚሠራ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚደንት አቶ ጌታቸው ረዳ ተናገሩ፡፡

ጊዜያዊ አስተዳደሩ ከደቡብ እና ምስራቃዊ ዞን ነዋሪዎች ጋር በመቐለ ከተማ ላይ በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ሰሞኑን ውይይት አድርጓል በውይይቱ ወቅት አቶ ጌታቸው እንዳሉት፤ የሕዝቡን የተደራጀ አቅም በመጠቀም በአጭር ጊዜ ውስጥ ጥቄዎችን ለመመለስ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

በጦርነት የተጎዳው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዘርፉ ወደ ተሻለ ሁኔታ መመለስ አለበት ያሉት አቶ ጌታቸው፤ በተለይ በግብርናው ዘርፍ ብዙ ክፍተቶች መሞላት እንዳለባቸውና፤ የጤና እና የትምህርት ዘርፉ ላይ በትኩረት መሠራት እንዳለበት አመልክተዋል፡፡

የክልሉ ማዕድን እና መሬት በተመለከተ የተሠሩ ወንጀሎች በአግባቡ ወደ ሕግ የሚቀርቡበት አካሄድ ይኖራል ያሉ ሲሆን፤ ይህንን ለማሳካት አስተዳደሩ በተስተካከለ የአሠራር መንገድ ይፈታዋል ብለዋል። በኢንቨስትመንት ዙሪያ አካባቢው ምቹ በማድረግ ያለውን ሀብት አልምቶ ህብረተሰቡ የሚጠቀምበትን ሁኔታ አስተዳደሩ እንደሚያመቻች አመልክተዋል፡፡

በክልሉ በሚገኙ ኢንቨስትመንቶች ላይ ወጣቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን የሚፃረር አሠራር ሲሠራ ቆይቷል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ይህ በአግባቡ ሥርዓት በማስያዝ ወጣቱን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፍትሃዊ የኢንቨስትመንት አሠራር በመዘርጋት ተግባራዊ እንደሚደረግ አስረድተዋል፡፡

በመድረኩም ላይ በተሳታፊዎች ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከል የሰላም ጅማሮ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እና የሰላም ድምፅ እንዲሰማ፣ በመጠለያ ውስጥ የሚገኙ ተፈናቃዮች ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ እና ከመሬት ጋር ተያይዞ በሕገ ወጥ መንገድ የሚዘረፈው መሬት እና ማዕድን እንዲቆም፤ በተጨማሪም ንፁህ የመጠጥ ውሃ እንዲሁም የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲስተካከል ይገኙበታል፡፡

ፕሬዚዳንቱ የተፈናቃዮች መመለስ በቀዳሚነት የተያዘ ጉዳይ መሆኑን ጠቅሰው፤ የነበረው ሰላማዊ መስተጋብር የሚመለስበት ፤ የክልሉ ቀጣይ ዓላማ ሰላምን በማስፈን ልማት ላይ ትኩረት እንደሚደረግ እና በስርቆትና በሙስና የሚታወቁ አስተዳዳሪዎች ላይ ሕጋዊ ርምጃ እንደሚወሰድ ገልፀዋል፡፡

በጥቅምት የሚኖረው እርጥበት በደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች ማሳን ለማዘጋጀት ምቹ ነው

ሄሰን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በጥቅምት ወር የሚኖረው እርጥበት በደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች ማሳን ቀድሞ ለማዘጋጀትና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት እኤአ ከጥቅምት አንድ እስከ ጥቅምት 31/2024 የሚኖረውን የአየር ሁኔታ ትንበያ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ አስታውቋል፡፡

በጥቅምት ወር በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸውና በሂደትም ወደ ደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል ብሏል፡፡

ይህም ሁኔታ ወቅታዊ ዝናብ ማግኘት በሚጀምሩትና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች ቀደም ብሎ የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ተመላክቷል፡፡

በተጨማሪም በአካባቢው ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው በመግለጫው አብራርቷል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ እርጥበቱ ቀጣይነት የሚኖረው በመሆኑ ቀደም ብለው ለተዘሩና አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ፣ በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ለመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ጉልህ ሚና እንዳለው ተጠቁሟል፡፡

የእርጥበት እጥረት ላለባቸው አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ለማቀብ እና ለማሰባሰብ ምቹ ሁኔታ ስለሚኖር ይህንኑ አጋጣሚ በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚያስፈልግ መግለጫው አስታውቋል፡፡

በሌላ በኩል በአብዛኛው የበጋ ወቅት እንደሚስተዋለው የሰሜን አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማ እና ነፋሻማ የአየር ጠባይ ጎልቶ ከመታየቱ አንጻር የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ መጨመር ያሳያል ተብሏል።

በጸሀይ ሃይል በመታገዝ ከሚጠናከሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመነሳት በጥቂት የምዕራብና በደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ተመላክቷል፡፡

በጥቅምት ወር ከአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ የእርጥበት ሁኔታው በመጠንም ሆነ በስርጭት እየቀነሰ እንደሚሄድ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

አብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ የታችኛውና የመካከለኛው ዓባይ፣ አሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ እስከ ከፍተኛ የሚደርስ የእርጥበት መጠን ያገኛሉ፡፡ ይህም የከርሰ ምድር እና የገፀ ምድር የውሃ ሀብትን ከማጎልበት አንጻር የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ተመላክቷል፡፡

በተጨማሪም የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦችን የውሃ መጠን ከፍ ስለሚያደርግ በመጪው የበጋ ደረቅ ወራት አስተማማኝ የሃይል አቅርቦት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር አወንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡

የታችኛውና የመካከለኛው ዋቢ ሸበሌ እና የገናሌ ዳዋ በአንጻሩ መጠነኛ የሆነ እርጥበት እንደሚያገኙም ተገልጿል፡፡

ርዕሰ አንቀፅ

በጋራ እጣ ፈንታ ላይ የተመሠረተው የኢትዮጵያ አሁናዊ እንቅስቃሴ የትናንቱ የነጻነት ትግል ቀጣይ ምዕራፍ ነው!

ከቅኝ ግዛት ማብቃያ ዋዜማ ጀምሮ አፍሪካውያን የራሳቸውን ዕጣ ፈንታ በራሳቸው ለመወሰን የሚያስችል የፓን አፍሪካኒዝም የፖለቲካ ኢኮኖሚ እሳቤ ፈጥረው ለተግባራዊነቱ ረጅም ርቀት ተጉዘዋል ። የነጻነት ትግሉን ያህል ውጤታማ ባይሆንም በየዘመኑ ለነበሩ እና ላሉ አፍሪካውያን ትውልዶች አስተሳሰቡ ራስን የመሆን መነቃቃት ምንጭ በመሆን እስካሁን ድረስ እያገለገለ ይገኛል።

የፓን አፍሪካኒዝም አስተሳሰብ አፍሪካውያን ያላቸውን አቅም አቀናጅተው በአንድነት /በህብረት መንቀሳቀስ ከቻሉ ፣ በብዙ የሕይወት መስዋእትነት ያገኙትን የፖለቲካ ነጻነት ፣ በኢኮኖሚው ዘርፍ በመድገም ፣ የተሟላ ነጻነት ባለቤት በመሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ በሁለንተናዊ መልኩ ተጠቃሚነታቸውንም ሆነ ተወዳዳሪነታቸውን የሚያጎለብት እንደሆነ በብዙ መልኩ አመኔታ ያተረፈ ነው።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቀደም ባሉት አባቶቻችን የተመሠረተው ፤ በኋለኛውም ዘመን ወደ አፍሪካ ህብረት የተሸጋገረው ይህንኑ ገዥ አፍሪካዊ የፖለቲካ- ኢኮኖሚ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ቢሆንም ፤ አስተሳሰቡ አስካሁን ድረስ በአህጉሪቱ የፖለቲካ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ውስጥ ስጋ እና ደም ተላብሶ አፍሪካውያን ተስፋ ያደረጉትን ውጤት ሊያመጣ አልቻለም ።

በአንድ በኩል የቀደሙ የቅኝ ግዛት አስተሳሰቦችን ዘመናዊ መልክ ተላብሰው የመምጣታቸው ሁኔታ እና እነሱን ተግባራዊ ለማድረግ በግልጽ ሆነ በስውር የሚደረጉ ጥረቶች እና በጥረቶቹ ውስጥ የተስተዋሉ ሴራዎች የነጻነት ትግሉን ያህል አፍሪካውያን በራሳቸው ጉዳይ በቁርጠኝነት በአንድነት እንዳይንቀሳቀሱ ፈተና ሆኖባቸው ቆይቷል።

የነጻነት ትግሉን ተከትሎ ዓለም የተጓዘችበት የተቃርኖ የፖለቲካ ኢኮኖሚ/ቀዝቃዛው ጦርነት ፤ አፍሪካውያን በራሳቸው እሳቤ እጣ ፈንታቸውን እንዳይወስኑ ፈተና ከመሆን ባለፈ ፤ በነጻነት ትግሉ ወቅት በመካከላቸው የተፈጠረውን አንድነትን እየሸረሸረው የተናጠል መንገድ እንዲከተሉ አስገድዷቸዋል። ይህን አንድነታቸው ሊፈጥር የሚችለውን አቅም እንዲያጡ እና በተናጠል ለሴራዎች የተጋለጡ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል ።

ከዚህም ባላፈ አንዳንድ ኃይሎች ከአፍሪካዊነታቸው ይልቅ ፤ ከበሬታ ከሰጡት አፍሪካዊ ካላልሆነው ማንነታቸው ጋር ከገቡት ተቃርኖ ጋር በተያያዘ ፤ ከአፍሪካውያን ወንድሞቻቸው የተለየ እጣ ፈንታ ያላቸው እስኪመስላቸው የሄዱበት ያልተገባ መንገድ ፤ ወንድማማችነትን በመሸርሸር አፍሪካውያንን ላልተገባ ጠላትነት ዳርገዋቸዋል ።

እነዚህ ኃይሎች አፍሪካዊ ወንድማማችነት ሊፈጥር ከሚችለው ወዳጅነት እና መተማመን ይልቅ ፤ ቅኝ ገዥዎች ለራሳቸው ጥቅም ላስቀመቸቸው ውሎች እና ውሎቹ ለተገዙላቸው አስተሳሰቦች ተገዥ በመሆን፤ የሕዝቦችን አንድነት፤ ከዚህ የሚመነጭ የጋራ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት አደጋ ውስጥ በሚከቱ ተግባራት ላይ በስፋት ሲንቀሳቀስ ማየት የተለመደ ሆኗል።

ይህ አፍሪካዊ ማንነትን እና ከዚህ የሚመነጨውን የጋራ እጣ ፈንታን ያለመቀበል የተሳሳተ አስተሳሰብ ፤ በተለይም በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ዘላቂ ሰላም እና መረጋጋት በማስፈን የሕዝቦችን የጋራ የልማ ት ተጠቃሚነት ተጨባጭ ለማድረግ የሚደረጉ ጥረቶች ስኬታማ እንዳይሆኑ ትልቅ ፈተና ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል።

ያልተገቡ ጥቅሞችን ለማስቀጠል ፤ ያልተገቡ ስጋቶችን ለመሻገር ፤ ከዚያም ባለፈ የሀገር ውስጥ የፖለቲካ አጀንዳዎችን ለመቀልበስ የሚደረጉ ጣልቃ ገብነቶች ፤ ባለፉት ስድስት አስርት ዓመታት ለአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ሀገራት እና ሕዝቦች የቱን ያህል ተግዳሮት እንደሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው ። ጣልቃ ገብነቱ ሀገራቱ እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ በግጭት አዙሪት ውስጥ እንዲያልፉ አድርጓል ፤ ጣልቃ ገብነቶች የፈጠሯቸው የልዩነት ትርክቶችም በፈጠሩት ተቃርኖ በመካከላቸው አለመተማመን እና ያልተገባ ባላንጣነት እንዲፈጠር እያደረገ ነው።

ዛሬም ኢትዮጵያ እንደ አንድ ኃላፊነት እንደሚሰማው ትልቅ ሀገር ፤ ከአካባቢው ሀገራት ጋር ያላትን አፍሪካዊ ወንድማማችነትን በማሳደግ ፤ የጋራ ተጠቃሚነት መሠረት ያደረገ አዲስ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የጀመረችው ጥረት በዚሁ የአህጉሪቱን ሕዝቦች ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት ሲፈታተን በነበረው የውጭ ጣልቃ ገብነት እየተፈተነ ይገኛል።

ለአፍሪካዊነታቸው ተገቢውን ከበሬታ በሌላቸው ኃይሎች የሚዘወረው ይህ ጣልቃ ገብነት ፤ ከሁሉም በላይ የአካባቢውን ሀገራት ሕዝቦች የሰላም እና የልማት ፍላጎት ታሳቢ ያላደረገ ፤በሴራ እና ሴራ በሚወልደው አለመረጋጋት እና ግጭት ተጠቃሚ መሆንን ተሳቢ ያደረገ ነው። ይህም እንደቀደሙት ዘመናት የአካባቢውን ሕዝቦች ያልተገባ ዋጋ ከማስከፈል ያለፈ ፋይዳ የሚኖረው አይሆንም።

የኢትዮጵያ መንግሥት እና ሕዝብ በአፍሪካዊነታቸው ብቻ ሳይሆን በአፍሪካዊ ማንነታቸው ከአካባቢው ሕዝቦች ጋር የጋራ እጣ ፈንታ እንደሚጋሩ የሚያምኑ ናቸው ፤ለዚህም በኃላፊነት መንፈስ የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ዘላቂ ከሆነ የጋራ ተጠቃሚነት ወንድማማችነትን ማስቀጠል እና ማጎልበት የሚፈልጉ ናቸው። አሁናዊ የፖለቲካ- ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎቻቸውም ይህንኑ እውነታ ታሳቢ ያደረጉ ናቸው።

ዓለም አቀፋዊ ሕጎችን ፤ የሞራል እሳቤዎችን እና ወንድማማችነትን ተሳቢ ያደረጉ ፤ ትናንት ለአፍሪካውያን የነጻነት ትግል ፋና ወጊ ሆነው ፤ለነጻነት ትግሉ መንፈሳዊ እና ሥነልቦናዊ አቅም እንደሆኑ ሁሉ፤ የፖለቲካ ነጻነቱን ምሉዕ በማድረግ ሂደት ፋና ወጊ በመሆን አህጉራዊ ብልጽግናን ማስፈን በሚያስችል ሀገራዊ መነቃቃት ውስጥ ናቸው።

ይህ ከፓን አፍሪካኒዝም የፖለቲካ -ኢኮኖሚ እሳቤ የሚመነጨው የኢትዮጵያ አሁናዊ እንቅስቃሴ ፤ የየትኛውንም ሀገር እና ሕዝብ ብሔራዊ ጥቅም የማይነካ ፤ እንደ ትናንቱ የነጻነት ትግል በአንድነት እና በኃላፊነት የጋራ እጣ ፈንታን ብሩህ የማድረግ ተልዕኮ ነው ። ተልዕኮው የመላው አፍሪካውያን የትናንት የነጻነት ትግል ቀጣይ ምዕራፍም ነው።

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpressproomotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

ለበዓሉ ሠላማዊነት ሁላችንም የሚጠበቅብንን ልንወጣ ይገባል

ክፍሰዮ ሐንስ አንበርብር

አዲስ አበባ በዚህ ሰሞኑን ውበቷ ጨምሯል። ከከተማዋ የኮሪደር ልማት በተጨማሪ የአዲስ ዓመት እና የመስቀል በዓልን መድረስ የሚያበስሩ መልካም ምኞት መገለጫዎች አሁንም ድረስ ውበታቸው እንደተጠበቀ ነው። ኢሬቻ ደግሞ የበለጠ ለከተማዋ ውበት እያላበሰ፤ አዲስ አበባ ወዘናዋ የደመቀ አዲስ የመስከረም ሙሽራ እያደረጋት ነው።

የከተማዋ በርካታ ህንፃዎች ሁሉ በእርጥብ ሣር ጎዝጓዝ እንደወዙ በአደይ አበባ እንዳሸበረቁም ይገናሉ። የከተማዋ ዓደባባዮች ደግሞ የተለያዩ ድምቀት ያላቸው በንፋስ የተሞሉ ፊኛዎች እና ሰንደቅ ዓላማዎች ሽብርቅ ብለዋል። ባህላዊ ሙዚቃዎች በየሰፈሩ እና በተለያዩ ተቋማት በር ላይ ከፍ ባለ ድምፅ ተለቀዋል።

በከተማዋ የተለያ አካባቢዎችም ወጣቶች እና ልጃገረዶችም የተለያዩ ባህላዊ ውዝዋዜዎችንና ትዕይንቶችን እያሳዩ ነው። ከተማዋ በሠላማዊ ድባብ ሠላማዊ ሰዎች እየተንሸራሸሩባት ነው። አዲስ ዓመት ይዞት ከሚመጣው ተስፋ ጋር ተዳምሮ፤ ከተማዋ በብዙ የተስፋ ጠረን ታውዳለች።

ከተማዋ በየዓመቱ የሚከበረውን የኢሬቻ በዓል ለማድመቅ በብዙ ዝግጅት ውስጥ ነች። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ እንግዶቿን እንኳን ደህና መጣችሁ ብላ በኢሬቻ በዓል አብራ ለመደሰት በሰፊው ደፋ ቀና እያለች ነው። ነዋሪዎቿም እንግዶችን ለመቀበል ፤እንኳን ደህና መጣችሁ ለማለት፤ በቀና መንፈስ የዝግጅቱ አካል ሆነዋል።

የኢሬቻ በዓል በዓመት ሁለት ጊዜ ክረምት ከመግባት በፊት እና ክረምት ከወጣ በኋላ የሚከበር ነው። የመጀመሪያው የኢሬቻ በዓል በተራራማ ሥፍራ ለምስጋና እና ቀጣይ ወራትን ስኬታማ እንዲሆን የሚመኙበት ነው። ሁለተኛው ደግሞ በሃይቅ እና ወንዞች አካባቢ ምስጋና ለማቅረብና ለቀጣይ ስኬትን ለመሻት የጎርፍ እና የጨለማን ወቅት አሻግሮ ለፀደዩ ብርሃን ላደረሰው ፈጣሪ ምስጋና የሚቀርብበት ነው።

ተደጋግሞ እንደተነገረው፤ በዓሉ ፍቅር፣ ሠላም፣ እርቅ እና አንድነትን የሚሰብክ፤ የኦሮሞ ማህበረሰብ አንድነቱን፣ ወንድማማችነቱን፣ ፍቅሩን፣ ብሔራዊ ኩራቱን፣ ታሪክና ባህሉን የሚገልፅበትና የሚያድስበት መድረክ ነው። ይህም ቢሆን የበዓል ሰሞን ዜማ ሊሆን አይገባም። ይህ ከሕዝቡ ጋር የኖረ እሴት በመሆኑ የበለጠ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው። ይሁንና ይህን እሴት የበለጠ ለማጉላት አጋጣሚዎችን መጠቀም አግባብ ነው።

ኢሬቻ ሲከበር ኦሮሞው ብቻ ሳይሆን ሌሎች በዓሉን ለመታደም የሚፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገኙበት ነው። በዚህ ሂደት ደግሞ ብዙ ማህበራዊ መስተጋብሮች የሚጠናከሩበት ነው። ይህም ሀገራዊ አንድነትን በማጠናከር ሂደት ውስጥ የሚኖረው ሥፍራ ከፍ ያለ ነው።

በአሁኑ ወቅት የቱሪዝም ኢንዱስትሪው ከሚያንቀሳቅሰው ከፍ ያለ ሀብት አካያ፤ ሀገራት ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን በስፋት እየተንቀሳቀሱ ነው፤ ሀገራችንን ከዘርፉ የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን በፖሊሲ የተደገፈ ሰፋፊ ሥራዎችን እየሠራች ነው። ከዚህ አኳያ ኢሬቻን በአግባቡ በማስተዋወቅ ተጠቃሚ መሆን የሚቻልበት ዕድል ሰፊ ነው።

ይህን በዓል ምክንያት ባደረገ እጅግ አስገራሚ የአልባሳት ዲዛይኖች፣ ባህላዊ ቁሳቁሶች እና የበዓሉ የድምቀት ምክንያት የሆኑ የዕደ ጥብ ውጤቶችን በሰፊው እየተመለከትን ነው። የቱባው ባህል ባለቤት የሆነው የኦሮሞ ሕዝብ በበዓሉ ወቅት የሚያሳያቸው የተለያዩ ትዕይነቶችም የዚሁ አካል ናቸው።

በዓሉ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ «ኢሬቼ ኢሬ ኬኛ» ወይንም በአቻ ትርጉሙ «ኢሬቻ ኃይላችን ነው» በሚል የበርካቶች መሰባሰቢያ ሆኗል። የበዓሉ ዋነኛ እሴት እንደተጠበቀ ሆኖ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ፋይዳዎችም አሁን አሁን ተገቢውን ግንዛቤ እያገኙ ነው።

ይህ በመሆኑም ቀደም ሲል ስለበዓሉ ግንዛቤው የሌላቸው አካላት እንኳን ሳይቀሩ ሲታደሙ መመልከት ጀምረናል። ይህም የመጣው ስለ በዓሉ ላለፉት ዓመታት

ኢሬቻ ሲከበር ኦሮሞው ብቻ ሳይሆን ሌሎች በዓሉን ለመታደም የሚፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገኙበት ነው:: በዚህ ሂደት ደግሞ ብዙ ማህበራዊ መስተጋብሮች የሚጠናከሩበት ነው:: ይህም ሀገራዊ አንድነትን በማጠናከር ሂደት ውስጥ የሚኖረው ሥፍራ ከፍ ያለ ነው

በተሠሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እንደሆነ ይታመናል።

በዓሉ የህብረተሰቡ የቆዩ ታሪካዊ መስተጋብሮች የበለጠ የሚጎለብትበት፣ እርቅና ሠላም የሚወርድበት፣ ሠላም እና አንድነት በፅኑ ቃላት የሚሰበክበትና የሚተገበርበት ከመሆኑ አንጻር፤ የሚመለከታቸው አካላት፤ በዓሉን ከማክበር ባለፈ ለበዓሉ እሴቶች የማስፋትን ሥራ የእያንዳንዷቷን የቤት ሥራ አድርገው ሊወስዱት ይገባል።

በበዓሉ ሰሞን የሚካሄዱ የባህል ሲንፖዚየሞች እና ባዛሮች በዓሉን ለመታደም የሚመጡ ብዛት ያላቸው የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ጎብኚዎች፤ ቆይታቸውን የበለጠ ትርጉም እና ትውስታ እንዲኖረው እያደረጉ ነው ፤ የባዛሮቹ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው እናዳለ ሆኑ እየፈጠሩት ያለው ማሕበራዊ መስተጋብርም ከፍያለ ነው።

በባህል ዘርፍ ላይ ጥናት የሚያካሂዱ ዓለም አቀፍ ምሁራን ሆኑ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎችም በርካታ ግብዓቶችን እያገኙበት ያለ የባህል ሲመንፖዚየሞችም የሀገሪቱን ህብረ ብሄራዊ ገጽታ ከማስተዋወቅ ባለፈ ለምርምር ተነሳሽነትን የሚፈጥሩ ናቸው።

ከዚህም ባለፈ ኢትዮጵያ የባህል አምባ ወይንም በባህል የታደለች ሀገር ብቻ ሳትሆን ያላትን ማቆየት የምትችል ሀገር መሆኗም በተጨባጭ ለዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ለማስተዋወቅ እንደ አንድ መልካም አጋጣሚ የሚታይ ነው።

ኢሬቻን የሚመስሉ በዓላት ካላቸው ሰፊ ጠቀሜታ በአኳያ መንግሥት መሰል ሕዝባዊ በዓላት በአግባቡ ተከብረው /ተጠብቀው/ እንዲቆዩ ልዩ ትኩረት ሊያደርግ፤ የበዓሉ ውበት የበለጠ እንዲጎለብት አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅበታል ።

በዓሉን ሊያከብሩም ሆነ ሊታደሙ የሚሰባሰቡ አካላትም አንዳቸው ከሌላኛው ያልተናነሰ ሀገራዊ ኃላፊነት አለባቸው። በዓሉ የጋራ ሀብት በመሆንም የበዓሉን አከባበር ሠላማዊ እንዲሆን መላው ሕዝባችን በይመለከተኛል መንፈስ በኃላፊነት መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።

ለበዓሉ ስኬታማነት እና ሠላማዊነትም የፀጥታ አካላትን መተባበር ፤ የበዓሉ ታዳሚዎችም እንቅፋት ሳይነካቸው፤ ንፋስ ሳይገባቸው ወደየመጡበት እንዲመለሱ ሁላችንም ትልቅ ኃላፊነት ፤ ይህንን ሃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ደግሞ በቂ ዝግጁነት መፍጠር ይጠበቅብናል ።

ፖለቲካና ወቅታዊ

ወቅታዊ

“ኢሬቻ የኦሮሞ ብቻ ሳይሆን የሌሎች ጥቁር ሕዝቦችም በዓል ነው”

- አቶ ሌኒን ቁጦ

በኦሮሚያ ስቴት ዩኒቨርሲቲ የባሕል እና የፎክሎር መምህር እና ተመራማሪ

ምሕረት ሞገስ

በኢትዮጵያ የክረምትን ማብቃት ተከትሎ የተለያዩ በዓላት ይከበራሉ። በሀገር ደረጃ የዘመን መለወጫ በዓል የሚከበር ቢሆንም፣ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ደግሞ በተለያዩ መልኩ በመስከረም ወር የየራሳቸውን በዓል ያከብራሉ። በማህበረሰብ ደረጃ በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት መካከል በኦሮሞ ማህበረሰብ የሚከበረው የኢሬቻ በዓል ዋነኛው ነው። ስመሆኑ ኢሬቻ ማለት ምን ማለት ነው? ስለምንነቱ የሚተነትኑ የተጠኑ ጥናቶች አሉ? ኢሬቻ መቼ ተጀመረ? የኢሬቻ በዓል አከባበር ምን ይመስላል? ኢሬቻ የእርቅ፣ የምስጋና እና የአብሮነት መገለጫ ነው የሚባለው ለምንድን ነው? ኢሬቻ ከኦሮሞ በዓልነት ባሻገር በምስራቅ አፍሪካ እና በአንዳንድ በሌሎችም የአፍሪካ ሀገሮች እንደሚከበር ይነገራል። እዚህ ላይ ምን ይላሉ? የሚሉትን እና ሌሎችም ጥያቄዎችን መሠረት አድርገን በኦሮሚያ ስቴት ዩኒቨርሲቲ የባሕል እና የፎክሎር መምህር እና ተመራማሪው አቶ ሌኒን ጉቶን አነጋግረናል።

«ኢሬቻ ሲነሳ በተጨባጭ መሬት ላይ ወርደን ስንመለከት፣ ከኩሽ ጋር ወይም ከኢትዮጵያውያን ጋር ብዙ ባሕልን የሚጋሩ ማህበረሰቦች አሉ። እኛ ኢትዮጵያውያንን ከኬንያ፣ ከሱማሊያ፣ ከብሩንዲ፣ ከሩዋንዳ ጋር ብዙ የሚያመሳስሉን ጉዳዮች አሉ። እነዚህ ሕዝቦች ወደ ኢሬቻ እየመጡ የበዓሉን አከባበር እያዩ ነው። የሚመጡት ተገደው፣ ተስምነው ወይም ተጠይቀው አይደለም። ስፖለቲካ ሳይሆን በኢሬቻ የበዓል አከባበር ውስጥ ራሳቸውን ስላዩ ነው። አጠቃላይ ኢሬቻ የኦሮሞ ብቻ ሳይሆን የመላው ጥቁር ሕዝብ ባሕል ነው።» ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህንን እና ሌሎች ምላሾችን ከሰጡን ከአቶ ሌኒን ጉቶ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል። መልካም ንባብ፡-

አዲስ ዘመን፡- ኢሬቻ ማለት ምን ማለት ነው?

አቶ ሌኒን፡- ኢሬቻ በአንድ ቃል ወይም በአንድ ዓረፍተ ነገር ይሔ ነው ብሎ ለመግለፅ ያስቸግራል። ትርጉሙ ብዙ ነው። በዋናነት ኢሬቻ ማለት ሳር ነው። ሳር (Coqorsa) የሚባል አለ። ሳሩ በጣም ጠንካራ እና በየትኛውም አካባቢ በማንኛውም አየር ጠባይ የሚበቅል ነው። በክረምትም ሆነ በበጋ አይጠወልግም፤ ወይም አይሞትም። ደጋም ሆነ ቆላ ላይ ይገኛል። ከክረምት እስከ ክረምት ይታያል። ኢሬቻ ለማክበር የሚኬደው ጫፉ ያልተቆረጠ ይህንን ሳር በመያዝ ነው። ይህ የሙሉነት ምልክት ነው። ከጨለማ ወደ ብርሃን መውጣትን፤ ምስጋና እና ጥጋብን ያመለክታል። የሰላም እና የእርቅም ምልክት ነው።

ሌላኛው የኢሬቻ ትርጉም ምስጋና ነው። ለምሳሌ የባሕል መድኃኒት የሚሰጡት የባሕል ሕክምና ባለሙያዎች “ጭሬሶታ” ይባላሉ። ድሮ በባሕላቸን በእነርሱ የዳኑ ለከብትም ለሰውም ኢሬቻ ይሰጣሉ፤ ለሀገሩ እና ለሳይኮሎጂው ለሁሉም ነገር ኢሬቻ ይሰጣሉ። እዚህ ላይ የምስጋና ስጦታ ነው ማለት ይቻላል። በኦሮሞ ባሕል ማንኛውም ሰው ቅዱስ ቦታ ላይ ሲደርስ ኢሬቻ ወይም ምስጋና ያቀርባል። ኢሬቻ በሁለት መልኩ ለሁለት ጊዜ ይካሄዳል። አንደኛው ኢሬቻ መልካ ሲሆን፤ ሁለተኛው ኢሬቻ ቱሉ ወይም ኢሬቻ “አፋታ” የምንለው ዝናብን ለመጥራት እና ክረምቱ የከፋ እንዳይሆን ተራራ አካባቢ ክረምቱ ከመምጣቱ በፊት የሚከናወን ነው።

ሌላኛው አንድ ሰው አንድ ጉዳይን በጥብቅ ከፈለገ እና ከተከለከለ፤ ኢሬቻ ወርውሮ ወይም ሰጥቶ ይጠይቃል። በዚህ ጊዜ ኢሬቻ ተሰጥቶት የተጠየቀ ሰው በምንም መልኩ አይከለከልም። ኢሬቻ የማክበር ምልክት ነው። ድመት እንኳ ከሞተች ትከበራለች። በላይዋ ላይ ኢሬቻ ይደረጋል። የሞተ ሁሉ መከበር አለበት የሚል እምነት በመኖሩ፤ የመቃብር ቦታም የኢሬቻ ቦታ ይባላል። በተጨማሪ አንድ ሰው ኢሬቻ ይዞ ሲሔድ ከታየ ለሰላም እና ለእርቅ እየሔደ መሆኑ ይታወቃል። እከሌ ኢሬቻ ይዞ ሔዶ ከተባለ ለእርቅ፣ ለሰላም፣ ለአንድነት እየሔደ መሆኑ ይታወቃል።

በደንብ መታወቅ ያለበት ኢሬቻ የኦሮሞ ባሕል ሆኖ በዓመት ሁለት ጊዜ ይከበራል። የአሁኑ መስከረም ላይ የሚካሔደው ኢሬቻ መልካ ወይም ኢሬቻ ብራ ይባላል። ይህ ኢሬቻ በኦሮሞ ዘንድ ክረምት ጨለማ ነው ተብሎ ስለሚታመን ከጨለማ እንኳን በሰላም አወጣኸን ለማለት የሚከበር ነው። በክረምት ምንም ነገር አይሰራም። በተለይ የበዓሉ መሪዎች ምንም አይሠሩም። የእርሻ ሥራ ይከናወናል፤ በተጨማሪ የግጦሽ ቦታ ይጠበቃል፤ ከዛ ውጭ ምንም ነገር አይሠራም። በክረምት ወንዝ ስለሚሞላ ዘመድ ዘመዱን መጠየቅ አይችልም። በክረምት ጊዜ ለሚበላው ነገር እንጂ ከዛ ውጭ ምንም አይሰራም። በክረምት ችግር እና ረሃብ ሊኖር ይችላል። ስለዚህ ክረምት ከባድ ነው ይባላል። ምንም ዓይነት ሠርግን ጨምሮ ድግስ አይደገስም። እንደውም የክረምትን ሞት ፈጣሪ ይከላከልልናል፤ የክረምትን ሠርግ ደጋሹ ይከለክላል የሚል ምሳሌያዊ አነጋገር አለ።

ይህን ተከትሎ የፀደይ ኢሬቻ የብራን ወቅት ተከትሎ የሚመጣ ስለሆነ “ቢራን ባሪኤ” ይባላል፤ ይህም ማለት ነጋልን ሁሉንም ነገር ማየት ቻልን ማለት ነው። ይህ ብራ ጊዜ በጉጉት ይጠበቃል። ሰዎች ለኢሬቻ አንድ ላይ ከወጡ በኋላ፤ የተዘራ ነገር ይደርሳል። ብራ ከሆነ ጥጋብ ነው። እንኳን ሰው ወፍም ይጠግባል። በፊት ወፍ እህል ይበላል ተብሎ አይጠበቅም። እንደውም ወፍ እንዳይበላ መከላከል በተቃራኒው ረሃብ ያመጣል ይባላል። ስለዚህ እነርሱም ይጥገቡ ይባላል። ክረምት አልፎ እንኳን በሰላም ተገናኘን ለማለት፤ ሰዎች ኢሬቻ ይዘው ወደ መልካ ወርደው በአንድነት በዓሉን ያከብራሉ። ሕፃን አዋቂው ሁሉም እንኳን በሰላም አደረሰን በመባባል ክረምቱን ይሸኛሉ።

ነገር ግን ሁለተኛው የተራራ ኢሬቻ (ኢሬቻ ቱሉ) የሚባለው ደግሞ ክረምቱ ሲመጣ ዝናቡ የሰላም እንዲሆን፤ ጉዳት እንዳይደርስ በረዶ እና መብረቅ እንዳይኖር ጸሎት ማድረግ ነው። ፈጣሪ የሚለመንበት በዓል ነው። ሥነ ሥርዓቱ ሰላማዊ ክረምትን መጥራት ሲሆን፤ ሁለቱም ኢሬቻ ላይ ሁሉም ማህበረሰብ ይሳተፋል። ጎላ ብሎ የሚታየው ግን የመልካ ኢሬቻ ነው። ሌላው ማንኛውም ሰው ወንዝ ጋር ሲደርስ ኢሬቻን ሳያከናውን አያልፍም። ለፈጣሪ ምስጋና አቅርቦ፤ የተቸገረውን ጥያቄ ለፈጣሪ ጠይቆ ያልፋል።

አዲስ ዘመን፡- ኢሬቻ መቼ እንደተጀመረ የሚያመላክቱ እና የሚተነትኑ የተጠኑ ጥናቶች አሉ?

አቶ ሌኒን፡- ተጨባጭ ነገር ባይሆንም ጥናቶች እንደሚያሳዩት ኢሬቻ የኦሮሞ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ሕዝብ ባሕል ነው። አንሸንት ኢጂብሺያን ከበፊት ጀምረው ኢሬቻን እንደሚያከብሩ የሚያመላክቱ ጥናቶች አሉ። ጉዳዩ ሄዶ ሄዶ የኩሽ ነገዶች የሚያከብሩት መሆኑን ያሳያል። ለምሳሌ ጨንበላላ ቃሉ ተለየ እንጂ ኢሬቻ ነው። ብዙ ጥናቶች እንደሚሳዩት ኢሬቻ ከ6 ሺህ 400 በላይ ዓመታትን አስቆጥሯል ሲሉ፤ የተወሰኑ ጥናቶች ደግሞ ዕድሜውን ወደ 12 ሺ ያሳድጉታል።

አዲስ ዘመን፡- የኢሬቻ በዓል አከባበር ምን ይመስላል?

አቶ ሌኒን፡- አከባበሩ የራሱ ሂደት አለው። መጀመሪያ የኢሬቻ ቀን ከመድረሱ ከሶስት ሳምንት በፊት አባገዳዎቹ ከሁሉም የኦሮሞ ጎሳዎች ስብሰባ ይጠራሉ። የሀገር ስብሰባ ተጠርቶ የኢሬቻ ሥነ ሥርዓት ሊከናወን ስለመሆኑ ይነገራል። ምን መደረግ እንዳለበት እና ምን መደረግ እንደሌለበት ምክክር ይካሄዳል። ከአንድ ቤተሰብ ጀምሮ በተለያየ መልኩ ያሉ ግጭቶች እንዲፈቱ፤ እርቅ እንዲወርድ፣ ለጎሳ ተወካዮች አደራ ይሰጣል። እርሱም አደራውን ይዘው ይገቡና በየአካባቢያቸው እና በየመንደሩ ያለውን ግጭት አይተው እና ሰምተው ኢሬቻ ሳይደርስ ግጭቶች እንዲፈቱ፤ እርቅ እንዲወርድ ያደርጋሉ።

ከአንድ ቤተሰብ ጀምሮ በተለያየ መልኩ ያሉ ግጭቶች እንዲፈቱ፤ እርቅ እንዲወርድ፣ ለጎሳ ተወካዮች አደራ ይሰጣል። እርሱም አደራውን ይዘው ይገቡና በየአካባቢያቸው እና በየመንደሩ ያለውን ግጭት አይተው እና ሰምተው ኢሬቻ ሳይደርስ ግጭቶች እንዲፈቱ፤ እርቅ እንዲወርድ ያደርጋሉ

በኢሬቻ ዋዜማ ደግሞ ሃጣሪ ወይም ቶልፈኖ የሚባል ሥርዓት አለ። ከየቀዬው ሰዎች ተጠራርተው በመውጣት አባ መልካ ማለትም የወንዙ ባለቤት በሆነ ሰው ተመርተው ኢሬቻ የሚከናወንበት የወንዝ ዳርቻ አካባቢ ያፀዳሉ። የማፅዳት ሂደቱ በአካል ብቻ ሳይሆን ኢሬቻ በሚከበርበት ቀን መጥፎ ነገር እንዳይፈጠር በመንፈስም ጭምር ያፀዳሉ። ማህበረሰቡ በዓሉን ደስ ብሎት እንዲያሳልፍ ከሌላ ቦታ መጥፎ ነገር መጥቶ ሕብረተሰቡን እንዳይጎዳ ለፈጣሪ ጥያቄ ያቀርባሉ።

ሁሉም ሰው በየአካባቢው ከራ ዲቁ የሚል ፕሮግራም ያካሔዳል። ይሄም መንገድ መጥረግ ማለት ነው። ማህበረሰቡ በሰላም የኢሬቻ ሥነ ሥርዓት ላይ እንዲሳተፍ እና በሰላም ሄዶ እንዲመለስ መንገድ ይጠረጋል። እዚህ ላይ «ሴቶች ለፈጣሪ ቅርብ ናቸው፤ ከወንዶች በላይ ሴቶች በፈጣሪ ተሰሚነትን ያገኛሉ።» ተብሎ ስለሚታመን የሴቶች ተሳትፎ ከፍተኛ ነው።

የበዓሉ ታዳሚ እሾህ ሳይወጋቸው፤ እንቅፋት ሳይመታቸው፤ ጉቶ ሳያደናቅፋቸው በሰላም ሄደው በሰላም እንዲመለሱ በዓሉን በደስታ እንዲያሳልፉ ሴቶች ለፈጣሪ ቀኑን አስመልክተው ጸሎት ያደርጋሉ። ከዛም ወደሚከበርበት ቦታ ይሄዳል። መጀመሪያ ያላገቡ ልጃገረዶች በሰልፍ የሚሔዱ ይሆናል። ልጃገረዶቹ ወዩ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

ወቅታዊ

“ኢሬቻ የኦሮሞ ብቻ ሳይሆን የሌሎች...

ከገጽ 6 የዞረ

ወይም ቅዱስ ይባላሉ። ፈጣሪ ልጃገረዶችን ይሰማል ተብሎ ይታመናል። ከዛ ያላገቡ ወንድ ልጆች ይሰለፋሉ። ያገቡ ሴቶች ፣ ሽማግሌዎች፣ ፎሌዎች ወይም ወጣቶች ከኋላ ሆነው «መሬሆ...፣ መሬሆ...» እያሉ ሁሉም መልካ ወይም የኢሬቻ ቦታ ላይ ሲደርሱ ኦፋ ወይም አራራ የሚል ሥነ ሥርዓት ይካሄዳል። ኦፋ ወይም አራራ ማለት እርቅ እንደማለት ነው።

ከተለያዩ ቦታዎች ከጎሳ ተወካዮች ሾልኮ የመጣ ግጭት ካለ፣ ቂም ይዞ ወደ በዓል ቦታው የመጣ ሰው ካለ፣ አባገዳዎች መልካ ወይም በዓሉ የሚከበርበት ቦታ አቅራቢያ ላይ ቆመው ይጠይቃሉ። በጎሳ፣ በቡድን ወይም በግለሰብ ደረጃ ያለ ቂም ወይም ግጭት ስለመኖሩና ስላለመኖሩ ጥያቄ ያቀርባሉ። እርቅ ሳይወርድ ቂም ይዘው ወደ መልካ ከመሔድ መቅረት ይሻላል ተብሎ ይታመናል። ቂም በልብ እና በሆድ ይዞ ኢሬቻ መሔድ ለህብረተሰቡም ሆነ ቂም ለያዘው ግለሰብ መጥፎ ነው ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ አባገዳ ወደ መልካ ሳይወርዱ «ሃቲ ዋቃን ነጋ? » በማለት ይጠይቃል። ከፈጣሪ ጋር ሰላም ነው? « ሃቲ ለፋን ነጋ?» ከመሬት ጋር ሰላም ነው? « ሃቲ ወሊን ነጋ? » ብለው ይጠይቃሉ።

የአባገዳዎቹ ጥያቄ ሰው ከሰው ጋር ወይም ሰው ከፈጣሪው ጋር ብቻ ሳይሆን ሰው ከራሱም ሆነ ከመላው ፍጥረት ጋር ሰላም መሆኑን በተመለከተ ይጠይቃሉ። የበዓሉ ታዳሚዎች «ነጋ» ሰላም እያሉ ይመልሳሉ። ቅሬታ ያለበት ደግሞ «ነጋ» አይልም፤ ቂም መያዙን ወይም መጋጨቱን እና አለመታረቁን ይናገራል። ከእከሌ ጋር ግጭት ውስጥ ነን ወይም እነ እከሌ ግጭታቸውን አልፈቱም ይላል። በዚህ ጊዜ እዛው ፊት ለፊት በግልፅ ጠብ ውስጥ የገቡት ወይም ቂም የያዙ ሰዎች ግጭታቸውን ፈትተው በመጨረሻም የእርቅ ሥነ ሥርዓት ከተካሄደ በኋላ፤ በድጋሚ « ሃቲ ዋቃን ነጋ? » ፤ « ሃቲ ለፋን ነጋ?»፤ « ሃቲ ወሊን ነጋ? » ሲባሉ አዲሶቹ እርቅ ፈፃሚዎቹም አብረው ሁሉም «ነጋ » ይላሉ። ሁሉም ከፈጣሪ ጋር፣ ከመሬት ጋር፣ ከሰው ጋር በአጠቃላይ ከሁሉም ፍጥረታት ጋር ሰላም ነኝ ብለው፤ ሰው እጁን ከተጨባበጠ እና እርቅ ወርዶ በመጨረሻም ወደ ምርቃት ይኬዳል።

በኢሬቻ መጀመሪያ ምርቃት የሚያደርገው አባ መልካ ነው። አባ መልካ ማለት የወንዙ ባለቤት ማለት ነው። በየአካባቢው « ይሄ ወንዝ የእከሌ ጎሳ ነው። ከእከሌ ጎሳ አንጋፋው ማን ነው? » የሚል ጥያቄ ይቀርባል። የዛ መልካ ባለቤት መጀመሪያ ምርቃት ይሰጣል። ከዛ እንደ ቅደም ተከተሉ አባ ገዳዎች ኢሬቻ ያደርጋሉ። ከአባ መልካ በፊት አባ ገዳዎችም ኢሬቻ አያደርጉም። ከፋቹ አባ መልካ ነው። ከእነርሱ ቀጥለው አባ ገዳዎች እና ልጃገረዶች ኢሬቻውን ያከናውናሉ። ሳር እና አደይ አበባ ይዘው በመሔድ ለሚቀጥለውም አድርሰን ብለው እዛው ያስቀምጣሉ። በኋላም ሴቶቹ ውሀውን በመቅዳት ልክ እንደ ፀበል ወደ ቤታቸው ይዘው ይሔዳሉ። ይህ ቤት ላሉ ሕፃናት እና በዓሉን ለማክበር ያልቻሉ አልጋ ላይ ላሉ አዛውንቶች ቤታቸው ድረስ ይወሰዱላቸዋል።

ይህ ምልክቱ (ሲምቦሉ) ማንኛውም ሰው አቅመ ደካሞች መንቀሳቀስ የማይችሉ ሁሉም ከኢሬቻ አልቀሩም ለማለት ነው። በኢሬቻ ቀን ሁሉም ፍጥረት ጠግቦ መብላት አለበት ተብሎ ይታመናል። በኢሬቻ ቀን ያልጠገበ ሰውም ሆነ ከብት ዓመቱን ሙሉ አይጠግብም ተብሎ ስለሚታመን ከብቶቹም ወደ ግጦሽ ተፈተው ይለቀቃሉ፤ እስከሚጠግቡ ይበላሉ። ልጆችም በደንብ ጠግበው መዋል አለባቸው ይባላል።

አዲስ ዘመን፡- ኢሬቻ የሰላም፣ የእርቅ እና የምስጋና እንዲሁም የአብሮነት መገለጫ ነው የሚባለው ስምንድን ነው?

አቶ ሴኒን፡- በኦሮሞ ባሕል መጀመሪያ አንድ ሰው ከራሱ ጋር ሰላም መሆን አለበት። ከሌላ ሰው ጋርም ሰላም መሆን አለበት። ሰው ካልሆኑ ፍጥረታት ጋርም ሰላም መሆን አለበት። እኛ ሰዎች ሰላም ስንሆን ከፈጣሪ ጋርም ሰላም እንሆናለን ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ ኢሬቻ በሰላም የጨለማውን ወቅት ከባዱን ጊዜ ያሳለፍከን ምስጋና ይገባሃል ብለው ሳሩን እህሉን የሰጠህን ለዚህ ቀን ያደረስከን ፈጣሪ ተመስገን ለማለት ነው። ለወደፊትም ሰላም እንዲኖር፤ በሽታ መጥቶ ማህበረሰቡ በወረርሽኝ እንዳይጎዳ ይፀለያል። እህል በሰፊው ሲኖር በሽታ ይመጣል

የሚል ፍራቻ አለ። በሽታ ሳይመጣ «ያመረትነውን በጋራ አብላን» ይባላል። እዚህ ላይ ስለአብሮነት ይነሳል።

በሌላ በኩል ኢሬቻ የአብሮነት መገለጫ ነው የሚባለው ኢሬቻን የሚያከብረው የእከሌ ጎሳ ነው ብቻ ተብሎ ስለማይወሰን ነው። ሁሉም በአብሮነት በዓሉን ያከብራል። ኢሬቻ ብቻ ሳይሆን ኦሮሞ በባህሪው አቃፊ ነው። ኢሬቻም የኦሮሞ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ ሁሉ ነው። ኢሬቻ የሚካሔደውም ለኦሮሞ ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ በሙሉ አልፎ ተርፎ ፍጥረታት ሰላም እንዲሆኑ የሚፀለይበት ነው። ተፈጥሮ ሚዛናዊ ሆና እንድትቅጥል ፈጣሪ የሚጠየቅበት ነው። ማንኛውም ሰው፤ ሌላውም ብሔረሰብ ኢሬቻ ላይ ሲሳተፍ ለምን መጣህ ተብሎ አይጠየቅም። ለምሳሌ ከሌላ ማህበረሰብ ጋር ያላለቁ ጉዳዮች ወይም ግጭቶች ካሉ ያ ማህበረሰብ ኢሬቻን ጠብቆ በዓሉ የሚከበርበት ቦታ ላይ በመገኘት እርቅ እንፈልጋለን ብለው ይጠይቃሉ። በኢሬቻ ስም ከመጡ ደግሞ ይሄ እንዲህ ስለሆነ አይመጣም ማለት አይቻልም። እንደውም ሽማግሌዎች ኢሬቻ የሁሉም የሰው ልጅ ሠርግ ነው ይላሉ።

ሌላው ኢሬቻ የሰላም ኦዲት ነው። አንዳንድ ጊዜ በሽምግልናም ያልታረቀ እና የተኮራረፈ ሰው በክረምት ወቅት ሰላም አውርዶ በኢሬቻ ወደ ብርሃን ሲሸጋገር ከፈጣሪ ጋር በሰላም ይገናኛል። ስለዚህ በኢሬቻ ሰላም፣ እርቅ እና አንድነት ጎልቶ ይወጣል። ሰዎችም ተገናኝተው ይጠያየቃሉ። ዋናው ጉዳይ የመስከረሙ ኢሬቻ ጎላ ብሎ የሚታየው ምስጋና ነው። የቱሉ ኢሬቻ ወይም የተራራው ኢሬቻ ደግሞ ለፈጣሪ ልመና የሚቀርብበት ነው። ሁሉም አንድ ላይ ሆኖ ለፈጣሪ ጥያቄ ያቀርባሉ።

አዲስ ዘመን፡- ኢሬቻ ከኦሮሞ በዓልነት ባሻገር በምስራቅ አፍሪካ እና በአንዳንድ በሌሎችም የአፍሪካ ሀገሮች እንደሚከበር ይነገራል። እዚህ ላይ ምን ይላሉ?

አቶ ሴኒን፡- ኢሬቻ የኦሮሞ ብቻ ሳይሆን የሌሎች ጥቁር ሕዝብም ባሕል ነው ማለት ይቻላል። ሁሉም ቦታ ምስራቅም ሆነ ምዕራብ አፍሪካ በሁሉም ቦታ በአፍሪካ ኢሬቻ ይከበራል። ነገር ግን ዘመናዊነት ወይም ከውጭ የመጡ ሃይማኖቶች ሳይገቡ በፊት አፍሪካ ውሀን በልዩ ሁኔታ ታያለች። ሁሉም ነገር የተፈጠረው ከውሃ ነው ተብሎ ይታመናል። በአፍሪካ ፍልስፍና « ውሀ ሕይወት ነው» ይባላል። ሁሉም ፍጥረታት መነሻቸው ውሀ ነው። የኦሮሞ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ትልቁ ቲዎሪ ውሀ ትልቅ ቦታ አለው። በዚህ ምክንያት በሩዋንዳ፣ በሌሎችም በጋና እና በዙምባብዌ ኢሬቻ ይከበራል።

አንደኛ እኛ የኩሽ ሕዝብ ነን። በተጨባጭ መሬት ላይ ሲወረድ በአፍሪካም ሆነ በዓለም ደረጃ ከኩሽ ጋር ወይም ከኢትዮጵያውያን ጋር ብዙ ባሕልን የሚጋሩ ማህበረሰቦች አሉ። ከኬኒያ፣ ከሱማሊያ፣ ከብሩንዲ፣ ከሩዋንዳ ወደ ኢሬቻ እየመጡ እያዩ ነው። የሚመጡት ለፖለቲካ ሳይሆን በኢሬቻ የበዓል አከባበር ውስጥ ራሳቸውን ስላዩ ነው። ተገደው፣ ተለምነው ወይም ተጠይቀው አይደለም። የራሳቸውን ባሕል ስለሚመስል ራሳቸውን ስለሚያዩ ነው። ስለዚህ ኢሬቻ የኦሮሞ ብቻ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያ፣ የአፍሪካ በአጠቃላይ የጥቁር ሕዝብ ፍልስፍና መሆኑን ብዙ ጥናቶች ያሳያሉ።

አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ ከኢሬቻ ጋር ተያይዞ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ ዕድሉን እንስጥዎ?

አቶ ሴኒን፡- ኢሬቻ እና ሌሎቹም በዓላት ዓመቶችን ብቻ በመጠበቅ ማክበር ተገቢ አይደለም። በእያንዳንዱ በዓላት ላይ ጥናት መካሔድ አለበት። ስለኢሬቻ በደንብ ተጠንቶ መረጃ የማቅረብ ችግር አለ። ኢሬቻ ላይ የሰዎች አረዳድ የተለያየ ነው። አንዳንዴም በተለያየ ምክንያት የተዛባ አመለካከት አለ። ሰዎች የሚረዱት በተለያየ መንገድ ነው። ኢሬቻ የሚከበረው ለምንድን ነው? የሚለውን በደንብ ማሳወቅ ይገባል። ይህንን ለኦሮሞ ብቻ ሳይሆን ለመላው ኢትዮጵያውያን አልፎ ተርፎ ለአፍሪካ ማሳወቅ ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ተገቢ ነው።

ኢሬቻ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በዓላትን በተመለከተ ጥናት የሚካሔድበት ማዕከል ማቋቋም ያስፈልጋል። ኢሬቻን ቱሪስቶች መጥተው እያዩት ነው። ለቱሪስቱም ሰፊ ትንታኔ ለመስጠት፣ በጽሑፍም ሆነ በተለያየ መንገድ ማለትም በዲጂታል ለዓለም ማህበረሰብ ስለኢሬቻ ለማሳወቅ እና በቀላሉ ለማግኘት በሚያመች መልኩ ለማስቀመጥ ጥናት ማካሔድ ያስፈልጋል።

ቀደም ሲል ኢሬቻ በኢኮኖሚው ላይ ያለው እንቅስቃሴ ውስን ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢኮኖሚ ውስጥም አስተዋፅኦ እያደረገ ነው። በየዓመቱ ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑን አይተናል። ለቱሪዝም መንቀሳቀስ አስተዋፅኦ እያደረገ ነው። በፊት የበዓሉ አከባሪዎች የሚጠጡት ውሃ እና የሚበሉትን ምግብ በቀላሉ ማግኘት አይችሉም ነበር። አሁን ግን እየተሻሻለ ሰዎች በበዓሉ ላይ እያቀረቡ ነው። ይህ ኢኮኖሚውን እያንቀሳቀሰው ነው። ስለዚህ ኢሬቻ ለአዲስ አበባ፣ ለቢሾፍቱ እና ለሌሎችም ከተሞች ያለው ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦ ምን ይመስላል? የቱሪዝም አቅሙስ ምን ያህል ነው? የሚሉት ጉዳዮች በደንብ ተጠንተው መታወቅ አለባቸው።

ሌላኛው ኢሬቻ ራሱን ችሎ ዩኔስኮ ላይ እንዲመዘገብ በምሁራን ማስጠናት ይገባል። ኢሬቻ የኦሮሞ ነበር፤ አሁን ግን የኢትዮጵያ፣ የአፍሪካ ሆኗል እንደውም የዓለምም ሆኗል ብሎ በማስቀመጥ ዩኔስኮ ላይ እንዲመዘገብ ማስቻል ይገባል።

በመጨረሻ ማለት የምፈልገው የበዓል አከባበር ሥርዓቱ ባሕሉን በጠበቀ መልኩ እንዲቀጥል ማስቻል ያስፈልጋል። ለምሳሌ ልጃገረዶች የሚይዙት ነገር አለ፤ ሽማግሌዎች እና ያገቡ ሴቶች እና ያገቡ ወንዶች ይዘው የሚሄዱት ነገር እና የአከባበር ሥርዓት አለ። በባሕሉ ስንቄን መያዝ የምትችለው ያገባች ሴት ናት። አሁን ላይ ግን ያላገባችም ይዛ ስትሔድ እየታየ ነው። ኦሮሮም የሚያዘው ባገባ ወንድ ብቻ መሆን ቢኖርበትም አሁን ያላገቡ ልጆችም ይዘው ሲሔዱ ይታያል። ይህ ጉዳይ በቶሎ መስተካከል አለበት።

አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም በጣም አመሰግናለሁ።

አቶ ሴኒን፡- እኔም አክብራችሁ ስለጋበዛችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ።

ኢሬቻ የኦሮሞ ብቻ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያ፣ የአፍሪካ በአጠቃላይ የጥቁር ሕዝብ ፍልስፍና መሆኑን ብዙ ጥናቶች ያሳያሉ

ወይዘሮ ፋጡማ ሁሴን

ወይዘሮ አሻ ሮባ

የኢሬቻ በዓል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸዋል።

በዘንድሮው ዓመት የባሌ፣ የወለጋ፣ የአርሲ፣ የጉጂ፣ የቦረና፣ የሸዋ እንዲሁም በተለያዩ የኦሮሞ አካባቢዎች የተለመዱ ባህላዊ አልባሳት በስፋት ለገበያ ማቅረባቸውን ይናገራሉ። የሁሉንም አካባቢ ባህል ያማከሉ አልባሳት በብዛት ከመቅረባቸው በላይ በጥራትና በዲዛይን የተሠሩ ናቸው ይላሉ።

በጥራትና በዲዛይን አማራጮች ላይ ትኩረት ያደረጉ አልባሳትና ጌጣጌጦች በመኖራቸው ሸማቾች ግብይት እየፈጸሙ መሆኑን ገልጸው፤ የባህል አልባሳቱ ዋጋ ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር ብዙ ጭማሪ እንዳላሳዩ እና ባህላዊ ይዘታቸውን በጠበቀ መልኩ በሸማኔ እንዲሁም በአልባሳት ባለሙያዎች ተዘጋጅተው መቅረባቸውን አመላክተዋል።

የወንዶች ባህላዊ ሸሚዞች ከ 700 እስከ አንድ ሺህ 200 ብር ለገበያ መቅረባቸውን አስረድረተው፤ የሴቶች ሙሉ አልባሳት ደግሞ ከሁለት ሺህ 500 እስከ አምስት ሺህ ብር ድረስ ገበያው ላይ እየተሸጠ መሆኑን ገልጸው፤ የኦሮሞ ባህላዊ አልባሳት በወርሃ መስከረም በኢሬቻ በዓል ወቅት ብቻ ሳይሆን ጋብቻ ፈጻሚ ጥንዶችም የባህል አልባሳት ተጠቃሚ መሆናቸውን ያብራራሉ፡፡

ለበዓሉ የሚቀርቡት አልባሳት የኦሮሞን ባህል አጉልተው ከማሳየታቸው በተጨማሪ የባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦችን ለምንሸጥ ነጋዴዎች ከፍተኛ የኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አስገኝተውልናል ብለዋል። ትውልዱ ባህሉ፣ እምነቱንና የቀደምት አባቶቹን የአለባበስ ሥርዓት ጠብቆ በማቆየት ረገድ ኢሬቻን የመሳሰሉ በዓላት የጎላ ሚና እንዳላቸውም ተናግረዋል፡፡

የቄሮን የቀሬን እንዲሁም የአባ ገዳን የአለባበስ ሥርዓት ጠብቀው የሚዘጋጁ የባህል አልባሳት ከጊዜ ወደ ጊዜ በአይነትም በብዛትም እየጨመሩ መጥተዋል ያሉት ደግሞ የኦሮሞ ባህል አልባሳት ነጋዴዋ ወይዘሮ አሻ ሮባ ናቸው፡፡ የለበሱት አልባሳት የኦሮሞ አርሲ አለባበስ መሆኑን ገልጸው፤ ሙሉ ልብሱ ከሁለት ሺህ 500 እስከ ሶስት ሺህ ብር ድረስ እንደሚሸጥ ገልጸዋል።

በየዓመቱ በመስከረም ሦስተኛ ቅዳሜና እሑድ ላይ የሚከበረው የኢሬቻ በዓል ዘንድሮ መስከረም 25 ቀን 2017 ዓ.ም. በአዲስ አበባ፣ በማግስቱ እሑድ በቢሾፍቱ ከተማ ይከበራል። የአዲስ አበባው በዓል «ኢሬቻ ሆረ-ፊንፊኔ» ሲባል፣ የቢሾፍቱው «ሆረ አርሰዲ» ይባላል፡፡

የኢትዮጵያን የዓመት መጀመርያ የሆነውን መስከረምን ከሚያደምቁት በዓላት አንዱ የሆነው ኢሬቻ፣ ከክረምት ወደ ብርሃን መውጣትን ምክንያት በማድረግ ምሥጋና የሚቀርብበት ሥነ ሥርዓት መሆኑ ይነገራል፡፡ የሚሞገሰው ልምላሜ ነውና ለምለም ቄጠማና አደይ አበባ እንዲሁም ባህላዊ አልባሳት የበዓሉ ልዩ መገለጫ ሆነው ይታያሉ፡፡

በአዲስ አበባ የተከፈተው ባዛር እና ኤግዚቢሽኑ ከነገ ጀምሮ እስከ መስከረም 24 ድረስ ይቆያል ተብሏል።

ማሻሻያው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ያልፈለጉ የመድሃኒት አስመጪ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ እንደሚሉት ከኢኮኖሚ ማሻሻያው በኋላ የተሻለ የዶላር አቅርቦት ቢኖርም አሁንም የምንፈልገውን መጠን ያህል ግን ማግኘት እየቻልን አይደለም ይላሉ፡፡

በቅርቡም መድሃኒት ለማስመጣት 200 ሺህ ዶላር ፈልገው ወደ ተለያዩ ባንኮች በተደጋጋሚ መሄዳቸውን ገልጸው፤ ነገር ግን ይህን ገንዘብ ሙሉ ለሙሉ የሚሰጣቸውን ባንክ አለማግኘታቸውን ይናገራሉ፡፡

ሥራ አስኪያጁ ከዚህ በፊት አስመጪዎች እቃ ሲያስመጡ የተወሰነ ክፍያ ፈጽመው ግማሹ እቃው ከገባ በኋላ የሚከፍሉበት አሠራር እንደነበር አስታውሰው፤ ከማሻሻያው በኋላ ባንኮች ዶላሩን ከብሄራዊ ባንክ ስለምንገዛ ሙሉ ክፍያ ፈጽሙልን እያሉ እየጠየቁን ነው፡፡ ይህም እቃው ሳይሸጥ ሙሉ ክፍያ መፈጸም ከባድ በመሆኑ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት አለመቻላቸውን ይገልጻሉ፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦቱን ከማሻሻል አኳያ ምን አስገኝቷል ስንል ቦንኮችንም ጠይቀናል፡፡ የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እመቤት መለሰ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ በቅርብ ጊዜ የተካሄደው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በባንኮች የውጭ ምንዛሬ ፍሰት ላይ ቀላል የማይባል ለውጥን አምጥቷል፡፡

ከዚህ በፊት በነበረው ፖሊሲ የውጭ ምንዛሬ በጥቁር ገበያ ላይ ሲዘዋወር የነበረ መሆኑን ጠቅሰው፤ አዲሱ ፖሊሲ ይህንን የገንዘብ ፍሰት በመቀነስ ገንዘቦች በሕጋዊ መንገድ ወደ ባንኮች እንዲመጡ እድል የፈጠረ ነው ይላሉ፡፡

በሀገሪቱ ከውጭ የሚመጡ ሸቀጦችና ዕቃዎች ሁሉ የተወሰነ የባንክ ምንዛሬ ፍቃድን ሽፋን በማድረግ ከጥቁር ገበያ በሚገዛ ምንዛሬ ይገባ የነበረ ነው የሚሉት ሥራ አስፈጻሚዋ፤ የአሁኑ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በጥቁር ገበያና በባንኮች ያለው የውጭ ምንዛሬ ዋጋ ተቀራራቢ እንዲሆን በማድረጉ የውጭ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች በባንኮች መመንዘር መጀመራቸውን ይገልጻሉ፡፡

በዚህም ወደ ባንኩ የሚመጣው የውጭ ምንዛሬ መጠን በመጨመሩ ከዚህ በፊት የነበረውን የውጭ ምንዛሬ እጥረት በተወሰነ መልኩ ማቃለል መቻሉን ይናገራሉ፡፡ ይህ ማለት ግን ችግሩ ሙሉ በሙሉ ተቀርፏል ማለት አይደለም የሚሉት ሥራ አስፈጻሚዋ፤ አሁንም የውጭ ምንዛሬ ክምችት በሚፈለገው ልክ አለመሆኑ ይገልጻሉ፡፡

ሌላኛው ሃሳባቸውን የሰጡት የእናት ባንክ የግብይት ተግባቦትና የደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክተር አክሊል ግርማ በበኩላቸው ባንኩ የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያውን ተከትሎ ሰዎች ሕጋዊውን የባንክ ሥርዓት እንዲጠቀሙ የተለያዩ ማስታወቂያዎችን ሲሠራ መቆየቱን አንስተዋል፡፡ በዚህም ጥሩ የሚባል የውጭ ምንዛሬ ፍሰት መኖሩና ከበፊቱ ጋር ሲነጻጸር ሰፊ የሚባል ልዩነት መስተዋሉን ይጠቅሳሉ፡፡ ዳይሬክተሩ ከበፊቱ የተሻለ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ይኑር እንጂ በሚፈልገው ደረጃ ማቅረብ ተችሏል ማለት አይቻልም ያሉ ሲሆን አስመጪዎች የሚጠይቁትን የውጭ ምንዛሬ አሁን በፍላጎታቸው ልክ ማቅረብ እየተቻለ አለመሆኑን ይናገራሉ፡፡

ለዚህም ብሄራዊ ባንክ ለሁሉም ባንኮች ጨረታ የማውጣት ሂደቱን ቢቀጥልና የባንኮች ውጭ ምንዛሬ ክምችት ከፍ እንዲል ቢሰራ የተሻለ መፍትሄ ይዞ ይመጣል የሚል ሃሳባቸውን አጋርተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ትናንት ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት፤ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም አካል የሆነውንና በቅርብ የተደረገውን የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያዎች አፈፃፀም ገምግመናል። ፖሊሲው ተፈፃሚ በሆነባቸው ሁለት ወራት የተረጋጋ የውጭ ምንዛሪ ከባቢን መመልከት መቻሉንም ነው የገለጹት።

በተመሳሳይም የገቢ ግባችንም የተቀመጠለትን ግብ በመምታት በታለመለት መንገድ ላይ ይገኛል ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)።

በአጠቃላይም ያለፉት ሁለት ወራት ፖሊሲው በስኬታማ አፈፃፀም ላይ መሆኑን አሳይተዋል ሲሉም ነው የገለጹት።

ተኪ ምርቶች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የዜጎች ኑሮ እየተሻሻለ፣ ድህነትም እየቀነሰ ይመጣል ይላሉ፡፡

አንድ ሀገር ሁሉንም ነገር አምርታ በራሷ መሸፈን የምትችልበት ሁኔታ አይኖርም የሚሉት አቶ ሙህዲን፤ ምግብና ምግብ ነክ፣ መድሃኒትና የጦር መሣሪያዎችን የመሳሰሉ ስትራቴጂክ ምርቶች ላይ ግን ራሷን ለመቻል መሥራት ይኖርባታል፡፡ ይህን ማድረግ የማትችል ከሆነ ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ሥርዓቱ ጫና እንዲያሳርፍበት ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚል ሃሳብ አላቸው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እንደ ሀገር ያለንን አቅም መለየትና ገቢ ምርቶችን መተካት፣ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ሆናም ምርቶቿን ለመሸጥ መሥራትም ለኢኮኖሚያዊ እድገት ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ ተኪ ምርቶች ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት የውጭ ምንዛሪ ለማዳን፣ ሠፊ የሥራ እድል ለመፍጠርና ዜጎች ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት እንዲችሉ ያደርጋል ይላሉ።

ተኪ ምርቶች እንዲጨምሩ የሀገሪቱን የምርትና ምርታማነት ማሳደግ እንደሚገባ የሚገልጹት ምሁሩ፤ መሠረተ ልማትን መዘርጋት፣ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፣ ፈጠራን ማሳደግ፣ ከዓለም አቀፉ ገበያ ጋር ትስስር መፍጠርና ያሉ እድሎችን አሟጦ መጠቀም እንዲሁም የገበያ ሥርዓቱን ጤናማና ዘመናዊ ማድረግ ይገባል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኢኮኖሚውን የሚመሩና የሚደግፉ ተቋማትን የመፈጸም አቅም ማሳደግ፣ የሚወጡ ሕግና ደንቦች ለሥራ ያላቸውን ምቹነት መፈተሽ ላይም መሥራት እንደሚገባ ይጠቁማሉ፡፡ የሚሠሩ ሥራዎች ዘላቂ ልማትን እንዲያረጋግጡ የሥራ አጥነት መቀነስ፣ የኑሮ ውድነቱ ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራትና የሀብት ፍትሐዊነትን ማጠናከር ያስፈልጋል ነው ያሉት፡፡

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህር አቶ ፍሬዘር ጥላሁን በበኩላቸው፤ በሀገር ውስጥ መመረት ሚችሉ በርካታ ምርቶችን ከውጭ እናስመጣለን፡፡ ይህም ሀገሪቱ በውጭ ምርቶች ላይ ጥገኛ እንድትሆን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እንድታወጣ ያደርጋታል። እናም ምርትና ምርታማነትን ማሳደግና ለፍጆታ የሚውሉ ምርቶችን ማምረት አንዱ የማክሮ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ ነው ይላሉ፡፡

የሀገር ውስጥ ምርቶች ተቀባይት እንዲጨምርም ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ከፍ ያለ ቀረጥ መጣልና የኮታ መጠን ማስቀመጥ እንደሚቻል የሚጠቁሙት ባለሙያው፤ ይህን ርምጃ ከመውሰዳችን በፊት ግን ያለውን አቅርቦትና ፍላጎት ማወቅ ያስፈልጋል። ከዚህም በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ሲመረቱ የሚያስወጡት ወጪ ከውጭ ከሚገቡበት የበለጠ ወጪ የሚያስወጣ አለመሆኑንም ማጥናት አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካት ስናስብ የምርቱን አዋጭነት፣ ቀጣይነትና ጥራቱን በሚፈለገው ልክ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ አመላክተው፤ ማህበረሰቡ ሀገራዊ ምርቶችን ገዝቶ መጠቀም ላይ ያለውን ፍላጎት ለማሳደግ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎች ላይ መሥራት ይጠበቅብናል ባይ ናቸው፡፡ አምራቾችም የሕብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ምርት ማምረት ይኖርባቸዋል ፡፡

እንደ ምሁራኑ ገለጻ፤ ሀገራዊ ምርትና ምርታማነት ስናሳድግ የሥራ እድል እንዲፈጠር፣ ምርቶችን በበቂ ሁኔታና በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ ያስችላል። የማህበረሰቡ ገቢ እንዲያድግና የኑሮ ሁኔታውም እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡

ሀገሪቱ ለገቢ ምርቶች የምታወጣውን ወጪ ለመቀነስ ተኪ ምርቶችን በብዛት፣ በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ ይህም በሀገሪቱ ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት እንዲመዘገብ የራሱን ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ኢኮኖሚ

ኢንቨስትመንት

ለሚ ናሽናል ሲሚንቶ - ለሲሚንቶ እጥረት ዘላቂ መፍትሄ የመስጠት ፋሬያማ ጥረት

አንተነህ ቸሬ

በኢትዮጵያ በከፍተኛ ፍጥነት እያደጉ ከሚገኙ ዘርፎች መካከል አንዱ የግንባታው (Construction) ዘርፍ ነው። ዘርፉ ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል በመፍጠርም ከፍተኛ ሚና ያለው ሲሆን፣ ከግብርና ቀጥሎ ከፍተኛውን የሰው ኃይል የያዘ በመባልም ይታወቃል። ይህ ዘርፍ በሌሎቹ የምጣኔ ሀብት ዘርፎች ውጤታማነት ላይም ቀጥተኛ ተፅዕኖ አለው። የግንባታው ዘርፍ እክል ሲገጥመው የግብርናውን ዘርፍ ጨምሮ የማምረቻና የአገልግሎት ዘርፎችም ለዚሁ ችግር ይጋለጣሉ።

የሀገሪቱ የኮንስትራክሽን ዘርፍ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በፈጣን እድገት ላይ ይገኝ የነበረ ቢሆንም፣ ኮቪድ፣ የሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነት፣ የግብአት እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ እጥረትና የመሳሰሉትን ተከትሎ መቀዛቀዝ ውስጥ መቆየቱም ይታወቃል። በዚህ ላይ ዘርፉ በበርካታ ችግሮች የተተበተበም ነው።

የዘርፉ ችግሮች ጠቅለል ተደርገው ሲገለፁ ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸው ጊዜና ዋጋ እንዲሁም በሚፈለገው ጥራት አለማጠናቀቅ በሚለው ከፍተት ላይ የሚያርፉ እንደሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልፃሉ። የአቅም ከፍተቶች መኖራቸው፣ ዓለም አቀፍ የገበያ ተለዋዋጭነት እንዲሁም ከዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች መማር አለመቻል ኢንዱስትሪው ተወዳዳሪ እንዳይሆን አድርገውታል።

በዘርፉ እድገት ላይ መሰናክል እየፈጠሩ ካሉ ግብዓቶች መካከል አንዱ የሲሚንቶ አቅርቦት እጥረትና የዋጋ መናር ነው። ምርቱን በተገቢው መንገድ ለገበያ ከማቅረብ ጋር የተያያዙ በርካታ ችግሮች አሉ። በሀገሪቱ የሚመረተው ሲሚንቶ ከፍላጎቱ ጋር መጣጣም አለመቻሉም ሌላው ችግር ነው። ከስምንት ሚሊዮን ኩንታል ብዙም ያልተሻገረው ዓመታዊ የፋብሪካዎች አጠቃላይ የማምረት አቅም ለሀገራዊ የሲሚንቶ ፍላጎት በቂ ምላሽ የሚሰጥ አይደለም።

በሲሚንቶ ፍላጎትና በአቅርቦት መካከል ያለው ልዩነት ሰፊ ሆኖ መቀጠሉ በዘርፉ እድገት ብሎም በሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ላይ ትልቅ ጫና አሳርፏል። ይህም አጠቃላይ የሲሚንቶ ገበያን ከማበላሸቱም በላይ ሲሚንቶ እጅግ በተጋነነ ዋጋ እንዲሸጥ ምክንያት ሆኗል። ያልተረጋጋው የሲሚንቶ ገበያ ለብዙ ፕሮጀክቶች መስተጓጎልና ወጪ መናር ትልቁን ድርሻ እንደሚይዝ ተገልጿል።

በየጊዜው ለሚከሰተው የሲሚንቶ እጥረትና የዋጋ መናር የተለያዩ ምክንያቶች ሲቀርቡና የመፍትሄ እርምጃዎችም ሲወሰዱ ቆይተዋል። ሲሚንቶ አምራቾች የመለዋወጫ እቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችል በቂ የውጭ ምንዛሬ እጥረት እና የመብራት መቆራረጥ በምርት ላይ ተፅዕኖ እንዳሳደረባቸው (በመብራት መጥፋት ምክንያት በ50 በመቶ እንዲያመርቱና ከሁለት ወራት በላይ ሳያመርቱ ለመቆየት መገደዳቸው) ሲገልፁ፣ መንግሥት በበኩሉ በሲሚንቶ ምርት ሂደት እያጋጠሙ ያሉ ማነቆዎችን በመለየትና ለችግሮቹ እልባት ለመስጠት እንዲሁም የአቅርቦት መጠንን በማሳደግ በገበያ ላይ የሚስተዋለውን እጥረት ለማቃለል የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ እርምጃዎችን ስለመውሰዱ መግለፁም ይታወሳል።

መንግሥት የሲሚንቶ እጥረትን ለመፍታት በአጭርና በመካከለኛ ጊዜ አማራጭነት ከወሰዳቸው እርምጃዎች በተጨማሪ፣ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ለማበጀት ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች ግንባታ ትኩረት ተሰጥቷል። ይህ የመንግሥት ትኩረት ፍሬያማ መሆን ጀምሯል። ግንባታው ተጠናቆ ባለፈው ሳምንት የተመረቀው ግዙፉ የ«ለሚ ናሽናል ሲሚንቶ» ፋብሪካም የዚሁ ማሳያ ነው።

በአማራ ክልል፣ ሰሜን ሸዋ ዞን፣ እንሳሮ ወረዳ፣ ለሚ ከተማ አቅራቢያ የሚገኘው ይህ ፋብሪካ፤ «ኢስት አፍሪካ ሆልዲንግስ» (East African Holdings S.C) በተባለ ሀገር በቀል ኩባንያ እና በቻይናው «ዌስት ኢንተርናሽናል ሆልዲንድ» (West International Holding) ሽርክና የተገነባ ነው። የፋብሪካውን ግንባታ ያከናወነው ደግሞ የቻይናው «ሲኖማ» ኩባንያ (Sinoma International Engineering) ነው።

ፋብሪካው በ187 ሔክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፣ ግንባታውም 600 ሚሊዮን ዶላር ፈጅቷል። በቀን 150 ሺህ ኩንታል ሲሚንቶ የሚያመርተው ይህ ፋብሪካ፣ በሀገሪቱ ያሉ ሁሉም የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ከሚያመርቱት ውስጥ ግማሹን ያህል የመሸፈን አቅም አለው። ከ20ሺ ለሚበልጡ ዜጎችም የስራ እድል ይፈጥራል።

መረጃዎች እንዳመለክቱት፤ ፋብሪካው በ187 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፣ ግንባታውም 600 ሚሊዮን ዶላር ፈጅቷል። በቀን 150 ሺህ ኩንታል ሲሚንቶ የሚያመርተው ይህ ፋብሪካ፣ በሀገሪቱ ያሉ ሁሉም የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ከሚያመርቱት ውስጥ ግማሹን ያህል የመሸፈን አቅም አለው። ከ20ሺ ለሚበልጡ ዜጎችም የስራ እድል ይፈጥራል። የሲሚንቶ ምርቱን ለማንቀሳቀስ በቀን እስከ 300 የሚደርሱ ባለ ተሳቢ ተሽከርካሪዎች ወደ ፋብሪካው ይገባሉ።

የአካባቢውን ብቻ ሳይሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ ባንኮችንና ሆቴሎችን ጨምሮ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ ነጋዴዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ባለሙያዎች እና ባለሀብቶችን በአጠቃላይ የሀገሪቱን ሕዝቦች ተጠቃሚ የሚያደርግ ዘመኑን የዋጀ ግዙፍ ፋብሪካ ነው። በአጠቃላይ የለሚ ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ሀገራዊ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ያሉት ታላቅ ፕሮጀክት ነው።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ፋብሪካው ከግዙፍነቱ በተጨማሪ በፍጥነትና በጥራት ተገንብቶ የተጠናቀቀ መሆኑን በፋብሪካው ምርቃ ሥነሥርዓት ላይ ተናግረዋል። እሳቸው እንዳሉት፣ ፋብሪካው ከጥሬ እቃ ጀምሮ ሁሉንም ነገር በሀገር ውስጥ የሚያሟላ ነው። አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ተደምረው ከሚያርቱት ግማሽ ገደማ ያህሉን ማምረት ይችላል።

«ባደጉ እና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት መካከል ያለው መሰረታዊ ልዩነት ከትናንት የወረሱት ወረት/ጥሪት እና እዳ ነው። ያደጉ ሀገራት ብዙ ወረት/ጥሪት ያካበቱ በመሆናቸው የሚገጥሟቸውን የዕለት ከዕለት ችግሮች በቀላሉ እየፈቱ መልካም ተቋማትንና ሀገርን ለትውልድ ማሸጋገር ይችላሉ። በአንፃሩ በርከት ያለ እዳ የወረሱ እና ብዙ ስብራቶች ያሉባቸው እንዲሁም ተቋማትን ያልገነቡ ሀገራት ድካማቸው ብዙ ስለሆነ ከፍ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶችን መገንባትና በጣም ፈጣን የሆነ አፈፃፀም ማስመዘገብ ካልቻሉ ችግሮቻቸውን በቀላሉ ሊፈቱ አይችሉም። ለዚህም ነው መንግሥት በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ትልቅ (ሜጋ)፣ ፈጣን እና ንፁህ የሚባሉ ሦስት መሰረታዊ ጉዳዮች መያዝ እንዳለባቸው የሚያምነው» ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም «ለሚ ፋብሪካን ያየ ሰው በመጠኑ ምን ያህል ግዙፍ እንደሆነ መገንዘብ ይችላል። ፋብሪካ ሳይሆን ፓርክ፣ ያማረ ከተማ መስሎ ፅድት ተደርጎ የተሰራ ነው። ሁለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ግዙፍና ንፁህ ፋብሪካ ሰርቶ ማጠናቀቅ መቻል ሙሉ በሙሉ ከመንግሥታችን ፍላጎትና እሳቤ ጋር የሚሄድ የተሳካ ስራ ነው። በተስማማነውና ቃል በገባነው እንዲሁም ‹ድህነትን ሳይሆን ብልፅግናን እናወርሳለን፣ የተሻለ ሀገር እናስረክባለን› ባልነው መሰረት፣ ጠንክርና ሰብሰብ ብለን ብንሰራ ሀገራችን ምን ልትመስል እንደምትችል ለሚ ሲሚንቶ ፋብሪካ ማሳያ እንደሚሆን እተማመናለሁ» በማለት ፋብሪካው በሀገር አቀፍ ደረጃ ትልቅ ትርጉም ያለው ግዙፍ ፕሮጀክት ስለመሆኑ አስረድተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ትኩረት ሰጥተው በንግግራቸው ካነሷቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ስለመንግሥትና የግሉ ዘርፍ ትብብር ነው። እንደሳቸው ገለፃ፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራት ትላልቅ ችግሮችና ስብራቶች አሏቸውና መፍትሄዎቻችን ትላልቅ መሆን አለባቸው። የኢትዮጵያ መንግሥት ግልጽ ፖሊሲ አለው። የኢትዮጵያን ችግር መንግሥት ብቻ ይፈታዋል ብሎ አያምንም። በመንግሥትና የግሉ ሴክተር ትብብር የኢትዮጵያ ችግር ባጠረ ጊዜ ሊቀረፍ እንደሚችል ያምናል። በመላው ዓለም የሚገኙ ገንዘብና እውቀት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ሀብታቸውን አስተባብረው ለኢትዮጵያ የብልጽግና ጉዞ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል።

«የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ ትብብር የኢትዮጵያን ስብራቶች በማስተካከል ተራሮቿን ሜዳ ለማድረግ ያስችላል። ገንዘብና እውቀት ያላችሁ እንዲሁም የስራ ትውውቅ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን ጊዜያችሁን አታባክኑ፤ ምቹ ፖሊሲ ስላለ ከያላችሁበት ስፍራ ገንዘባችሁንና እውቀታችሁን ይዛችሁ እንደአቶ ብዙአየሁ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በፍጥነት በመስራት ኢትዮጵያን በማልማት እንድትተጉ አደራ እላለሁ። ከዘገያችሁ ግን ጊዜ ያልፋል፤ ጊዜ ካለፈ ደግሞ ገንዘብና እውቀት ቢኖር እንኳ ጉልበት ስለማይኖር እንደዚህ ያለ መልካም ስራ ሰርቶ ማለፍ አስቸጋሪ ይሆናል» በማለት አሳስበዋል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ የፋብሪካውን ግንባታ መጠናቀቅ አስመልክቶ ባስተላለፉት መልዕክት፣ የለሚ ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ ለኮንስትራክሽን ዘርፉ ትልቅ አቅም የሚፈጥር ድንቅ ፕሮጀክት መሆኑን ጠቁመዋል። «የለሚ ናሽናል ሲሚንቶ ፕሮጀክት ነገ ልንገነባት ለምናስባት ኢትዮጵያ ድልድይ ሆነው ከሚያገናኙን በርካታ ታሪካዊ ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ ነው። ፕሮጀክቱ ነገ ልንገነባት ለምናስባት ኢትዮጵያ ድልድይ ሆነው ከሚያገናኙን በርካታ ታሪካዊ ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ ነው። ይህ ፋብሪካ በቀጣይም የሀገራችንን የሲሚንቶ ፍላጎት በማሟላቱ ረገድ፣ እንዲሁም የግንባታው ዘርፍ እንዲፋጠንና የመሰረተ ልማት ፍላጎታችንን ዕውን ከማድረግ አኳያ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል» ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም አቶ ተመስገን ከወራት በፊት የፋብሪካውን ግንባታ በጎበኙበት ወቅት፣ ግንባታው ሲጠናቀቅ ለኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ልማት የማይተካ ሚና እንደሚጫወት ገልፀው ነበር። «የፋብሪካው መገንባት የአካባቢው ኅብረተሰብ በስራ እድል ፈጠራ ግንባር ቀደም ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል። በሀገር ደረጃ ያለውን የሲሚንቶ እጥረትን ለማቃለልና ዋጋውን ለማረጋጋት ቁልፍ ሚና ይኖረዋል» በማለት ተናግረው ነበር።

የ«ኢስት አፍሪካ ሆልዲንግሥ» የቦርድ ሊቀ-መንበር አቶ ብዙአየሁ ታደለ ከወራት በፊት የፋብሪካ ግንባታው ዋና ሥራ የተባለው የማሽነሪ ተከላ መጠናቀቁ በተገለፀበት ወቅት፣ ግንባታው በከፍተኛ ፍጥነትና ጥራት የተከናወነው የመንግሥትን ድጋፍ በማግኘቱ እንደሆነ ተናግረው ነበር። «የፕሮጀክቶችን እለታዊ እንቅስቃሴ የሚከታተል አካል በመንግሥት ተቋቁሞ እየደገፈን ይገኛል። በዚህም ምክንያት ፋብሪካው በከፍተኛ ፍጥነትና ጥራት ተገንብቷል። ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት አጋዥ የተስፋ ብርሃን ሆኗል» ብለዋል።

የለሚ ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ ግንባታ እውን ካደረጋቸው ተሞክሮዎችና ካስገኛቸው ልምዶች መካከል አንዱ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ኩባንያዎች ሽርክና (Joint-Venture) የማከናወን ተግባርን ነው። በኢትዮጵያ መንግሥት ድጋፍ በኢትዮጵያና በቻይና ኩባንያዎች ሽርክና የተገነባው የለሚ ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ፣ ግዙፍ የልማት ፕሮጀክቶችን በሽርክና የማከናወን ዓይነተኛ ማሳያ ሆኗል።

መሰል የሽርክና ስራዎች የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የቴክኖሎጂ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ እድል ከመፍጠሩም በላይ፣ ዘመናዊ የፕሮጀክት አስተዳደር ስርዓቶችን ለመተግበር የሚስችላቸውን አቅም እንዲፈጥሩም ያስችላቸዋል። የቴክኖሎጂ ሽግግር የምርት ተግባራት በቴክኖሎጂ የታገዙ እንዲሆኑ ያደርጋል። በዚህም የምርት ስራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ እገዛ ያደርጋል።

በሀገር ውስጥና በውጭ ኩባንያዎች ሽርክና የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ከምርትና ግብይት፣ ከስራ እድል ፈጠራ እና ከቴክኖሎጂ ሽግግር ባሻገር ለሀገራት ምጣኔ ሀብታዊ ትስስር መጠናከርም ቀላል የማይባል አስተዋፅዖ እንዳላቸው የምጣኔ ሃብት ሳይንስ ጥናቶች ያሳያሉ። በዓለም አቀፍ የፕሮጀክት አስተዳደር የጥናት መጽሔት ላይ በታተመ ጥናት እንደተጠቆመው፣ የሽርክና ፕሮጀክቶች ለዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትና የገበያ እድል ፈጠራ ትልቅ ሚና አላቸው። ፕሮጀክቶቹ የባለድርሻዎቹን ልዩ ልዩ አቅሞችን በመጠቀም የተሻለ ጥራት ያለው ምርትና አገልግሎት ለመስጠት ያስችላሉ። ይህም በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ሰፋ ያለ የገበያ እድል እንዲያገኙ እድል ይፈጥርላቸዋል።

በተለይም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚሰማሩ ኩባንያዎች የውጭና የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች በሽርክና የሚሰሩበት የቢዝነስ ሞዴል እድገት እያሳየ እንደሆነ ጠቋሚዎች ናቸው። ይህም የሀገር በቀል ኩባንያዎች የማምረት አቅም አድጎ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ተወዳዳሪ የመሆን አቅማቸው ውጤት እያስመዘገበ እንደሆነ አመላካች ተደርጎም ይወሰዳል።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

ጎጣ

የመንግሥት ተቋማት የኑሮ ውድነቱን ለምን ያባብሳሉ?

አሲሴሮ

ኢትዮጵያም ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገራት በሚታረስ የእርሻ መሬትና በግብርና ምርት ቀዳሚ ሀገር ናት። ሆኖም በተቃራኒው የግብርና ምርቶችና ሌሎች መሰረታዊ አቅርቦቶች እጥረት ካለባቸውና ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ከሚታይባቸው ሀገራትም አንዷ ናት።

በአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣምና በተለያዩ ብልሹ አሰራሮች ምክንያት በየቀኑ እየጨመረ የሚሄደውም የሸቀጦች ዋጋ መናር በዜጋው ላይ ከፍተኛ የኑሮ ውድነትን በመፍጠር ህዝቡን ለምሬት እየዳረገው ነው። እንደሽምጥ ፈረስ የሚጋልበው የኑሮ ውድነት በተለይም ዝቅተኛውን የህብረተሰብ ክፍል ከሚሸከመው በላይ ሆኖበታል።

በተለይም ኅብረተሰቡ በዕለት ተዕለት በሚጠቀምባቸው መሰረታዊ ፍጆታዎች ላይ እየታየ ያለው የዋጋ ንረት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዜጎችን ህይወት እጅግ እየተፈታተነው ይገኛል። በእህል፣ በጥራጥሬ፤ በአትክልት ምርቶች፤ በግንባታ ዕቃዎች እና በመንግሥት አገልግሎቶች ላይ የዋጋ ጭማሪው አሳሳቢ ሆኗል። ነገሩን ይበልጥ ከባድ የሚያደርገው ደግሞ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ እያደረጉት ያለው የመንግሥት ተቋማት መሆናቸው ነው። በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሪፎርም ከተደረገበት ካለፉት ሁለት ወራት ወዲህ በርካታ የመንግሥት ተቋማት በየፊናቸው የዋጋ ጭማሪ እየደረጉ ነው።

የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርሙ በተደረገ ማግስት የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን በአንድ ኪሎ ስኳር ላይ ከ10 ብር ያላነሰ ጭማሪ አድርጓል። የኢምግሬሽንና ስደተኞች አገልግሎት በሁለት ሺ ብር ሲሰጥ የነበረውን የፓስፖርት አገልግሎት እስከ 25ሺ ብር አሳድጓል። ሰሞኑን የትራንስፖርት ባለስልጣን መንጃ ፈቃድ ለማውጣትና እና ለዕድሳት እስከ 100 ፐርሰንት ጭማሪ እስከማድረግ ደርሷል። በቦሎ እድሳት ላይም የተጨመረው ገንዘብ ብዙዎች እጃቸውን እራሳቸው ላይ እንዲጭኙ አድርጓቸዋል።

ይህ አልበቃ ብሎ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም በአገልግሎቴ ላይ ቫት ማሰብ እጀምራለሁ ማለቱ ህዝቡ ያስቀመጠውን ገንዘብ እንኳን በተመጣጣኝ ገንዘብ ማንቀሳቀስ እንደማይችል ያመላከተ ነው። ንግድ ባንክ በአገልግሎትና በአዳዲስ ፈጠራዎች ከሌሎች ባንኮች ጋር ተወዳዳሪ መሆን ሲገባው በረባ ባልረባው የአገልግሎት ክፍያ መጨመሩ ደንበኞችን የሚያርቅ ነው።

ከመንግሥት አገልግሎት መናር ጎን ለጎን በየቀኑና በየሰዓቱ የሚጨምረው የሸቀጦች ዋጋ በተለይም ዝቅተኛው የህብረተሰብ ክፍል ኑሮ እንደምርጊት እንዲከብደው ምክንያት ሆኗል። መሽቶ በነጋ ቁጥር «ከገበያ ጠፍተዋል»፤«ዋጋ ጨምሯል» የሚሉት አገላለጾች ኅብረተሰቡን በሰቆቃ ውስጥ እንዲኖር እያደረጉት ነው።

በመንግሥት ዘንድ የኢትዮጵያን ምጣኔ ሀብት ከፍተኛ ፈተና እየገጠመው ያለው ከዋጋ ግሽበት በተያያዘ መሆኑን በተደጋጋሚ ሲገለጽ ቢሰማም ችግሩን ለመቅረፍ የተኬደበት ርቀት ውጤታማ አለመሆኑ በየሰዓቱ የሚጨምረው የሸቀጦች ዋጋ መናር በቂ ማሳያ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ የመንግሥት ተቋማት ችግሩ አባባሽ ሆነው መገኘታቸው አነጋጋሪ ሆኗል።

ምግብ ነክ የሆኑና መሠረታዊነታቸው የታመነባቸው የፍጆታ ዕቃዎች በፍራንኮ ቫሉታ አሠራር ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ እና የመድኃኒት፣ ነዳጅ፣ ማዳበርያ፣ ዘይት እና ሌሎችም መሠረታዊ ሸቀጦች ግዢ አቅርቦት አቅርቦት እንዲቀላጠፍ የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል ቢባልም የኑሮ

የመንግሥት ተቋማት ኑሮ ማረጋጋት እና ኅብረተሰቡንም ከምዝበራ መታደግ ሲገባቸው ራሳቸው እየተሸቀዳደሙ የዋጋ ጭማሪ ማድረጋቸው ተቋማቱ የተቋቋሙበትን አላማ እንድንመረምር የሚያደርገን ነው

ውድነቱን ከመገስገስ ያቆመው አንዳች ምድራዊ ኃይል አልተገኘም።

ከዚሁ ጎን ለጎን በኢትዮጵያ ባለፉት አራት አመታት በተሰሩ የግብርናውን የማዘመን ስራዎች በሀገሪቱ ምርታማነት እንደጨመረ ቢታመንም በተለያዩ ህገወጥ አሰራሮችና የቁጥጥር መላላት ምክንያት ምርቱ ሸማቹ ህብረተሰብ ጋር በቀላሉ ለመድረስ ካለመቻሉም ባሻገር የዋጋ ንረትም እንዲከሰት ምክንያት ሆኗል።

በሂደት ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ መሻሻል አይነተኛ ሚና እንደሚጫወት የታመነበት የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርምን አላግባብ ትርጉም በመስጠት እላፊ ተጠቃሚ ለመሆን የሚሯሯጡ ነጋዴዎችና ተቋማት ታይተዋል። ከማሻሻያው በኋላ በምርቶችና ሸቀጦች ላይ ከፍተኛ ጭማሪ ታይቷል። በመሳለሚያና በመርካቶ አካባቢ ያሉ ነጋዴዎች እንደሚናገሩትም በነሃሲና መስከረም ወራት በጤፍ፤ በዱቄት፤ በፓስታና መኮረኒ ላይ የታየው የዋጋ ጭማሪ አስደንጋጭ ነው። ጤፍ በአንድ ወር ብቻ እስከ ሁለት ሺህ ብር ጭማሪ አሳይቷል። ፓስታና መኮረኒ ላይ በአንድ ወር ብቻ እስከ 30 ብር ጭማሪ ታይቷል።

ሆኖም በአሳሳቢ ሁኔታ የኅብረተሰቡን ጫንቃ እያነበጠ ያለውን የኑሮ ውድነት አሳስቦት ተገቢ የሆነ መፍትሄ ለማፈላለግ የሚተጋ ተቋም ማግኘት በጨለማ ውስጥ ጥቁር ድመትን የመፈለግ ያህል ከባድ እየሆነ መጥቷል። የመንግሥት ኃላፊዎች እና የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶችም የችግሩን አሳሳቢነት ከመቀበል ይልቅ አንዱ ወደ አንዱ እየወረወሩ ችግሩ መፍትሄ አልባ ሆኗል።

የኑሮ ውድነቱ አንዱ የታዳጊ ሀገራት ፈተና ነው። ኢትዮጵያም የዚሁ ችግር ሰለባ ነች። ከወር እስከ ወር ከዓመት እስከ ዓመት በየጊዜው ማሻቀቡና ተባብሶ መቀጠሉን የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት በየጊዜው የሚያወጣቸው መረጃዎችና በማኅበረሰቡ ላይ የሚታየው የኑሮ ጫና ያመላክታል። በየጊዜው እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ወድነት አሁን ላይ በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የማኅበረሰብ ክፍል በእጅጉ እየፈተነ ይገኛል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች እንደሚሉት፣ የኑሮ ውድነት ተከሠተ የሚባለው የማኅበረሰቡ የመግዛት አቅም ወይም ገቢ ማነስ ከዋጋ ግሽበት ጋር ተደምሮ የሚፈጥረው የመግዛት አቅም ሲዳከም ነው። በኢትዮጵያ ከመሠረታዊ የምግብ ፍጆታዎች እስከ ሌሎች ቁሳቁሶች ድረስ የዋጋ ግሽበቱ በየጊዜው እያሻቀበ ቢሆንም፣ የአብዛኛው የማኅበረሰቡ ክፍል ገቢ ወይም የመግዛት አቅም ግን ከዋጋ ግሽበቱ እኩል ማደግ አለመቻሉን የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ።

ለዋጋ ግሽበት ዋነኛ ምክንያቶች ከሚባሉት መካከል የአቅርቦት እና ፍላጎት አለመመጣጠን፣ የገበያ ምኅዳር ብልሽት ወይም ሕገ ወጥ ደላሎች በገበያ ውስጥ የሚፈጥሩት ጣልቃ ገብነት እና የጥሬ ገንዘብ ሥርጭት መብዛት በቀዳሚነት የሚነሱ መሆናቸውን የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። በኢትዮጵያ እየታየ ላለው የዋጋ ግሽበት ዋና ምክንያት ሆኖ የሚጠቀሰው የምግብ ነክ ሸቀጦች፣ በተለይ የእህል ዋጋ መናር ነው። ለዚህ ደግሞ የምርት እጥረት እና ተመርተውም ምርት በጸጥታ እና በግብይት ሰንሰለት መርዘም ወደ ህብረተሰቡ በበቂ ሁኔታ አለመድረስ ተጠቃሾች ናቸው።

በእርግጥ የኢትዮጵያ አመታዊ የምርት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ መሻሻል እያሳየ ነው። ከአምስት አመታት በፊት ከ300 ሚሊዮን ብዙም ከፍ የማይለው አመታዊ ምርት ዘንድሮ ወደ 800 ሚሊዮን አድጓል። ሆኖም አሁንም ቢሆን እያደገ ካለው የህዝብ ቁጥር አንጻር ገና ብዙ መስራት ይጠይቃል።

ለአገሪቱ የዋጋ ግሽበት የምርት እጥረት ብቻ የሚፈጥረው አይደለም። የዘመናዊ ግብይት ዕጦት እና የደላሎችና ህገወጥ ነጋዴዎች መበራከት ለችግሩ መባባስ መንስዔ ናቸው። የኢትዮጵያ ገበያ 200 እና 300 በመቶ ትርፍ የሚያዝበት ነው። ይህ በዓለም ላይ የለም። ይኼ አካሄድም በፖሊሲ ጭምር ታግዞ ሊስተካከል ይገባል።

የአገሪቷ ገበያ ሥርዓት ዘመናዊ ባለመሆኑ የፖሊሲ ለውጥ አስፈልጎታል። ይህንን መነሻ በማድረግ ከሁለት ወራት በፊት መንግሥት ወደ ትግበራ ያስገባው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ስርዓትም ለዚህ ሁነኛ መፍትሄ ይዞ ይመጣል ተብሎ ይጠበቃል። በሀገራችን ውስብስብና ኋላ ቀር የሆነ፣ የገበያ ስርጭት ነው ያለው። አንዳንድ ቦታ እንዲያውም በሞኖፖል የተያዘ ይመስላል። በተለይ ሸቀጣ ሸቀጥ ላይ ገበያው በሞኖፖል ተይዟል። ስለዚህ ይህንን በመፍታት አዳዲስ ኩባንያዎችን በማስገባት የውድድር ሜዳውን በማስፋት ረገድ ትልቅ ዕድል እንደሚፈጥር ታምኖበታል። ዘርፉን ለሚቀላቀሉ የሀገር ውስጥና የውጭ አዳዲስ ኩባንያዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ድጋፍ ከተደረገ በአንድ ቀን አዳር ዋጋ የተጋነነ ዋጋ በመጨመር ራሳቸውን ሚሊየነር ለማድረግ የሚጥሩት ስግብግብ ነጋዴዎች ከእንግዲህ ወዲያ ቦታ አይኖራቸውም።

ይህ አካሄድም በውድድር ዋጋ የሚቀንስበትን መንገድ በመፍጠር የኑሮ ውድነቱ እንዲረጋጋ ያደርጋል። ቀልጣፋ የሆነ አቅርቦትና ውድድር ከተፈጠረ የዋጋ ግሽበቱን መቀነስ ይቻላል። አዲሱ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያም ሁሉም ነገር በገበያ እንዲወሰን በር ስለከፈተ በጥቂት ነጋዴዎች ተይዘው የቆዩ ዘርፎችም በርካታ ተዋናዮች እንዲኖሩ በማድረግ ሸማቹ በርካታ አማራጮች እንዲኖሩት ያስችላል።

ግሽበቱን ለመቀነስ በቂ ምርት ሊኖር ይገባል ከተባለ ደግሞ ሸማቾች የሚጠቀሙባቸው ከአገር ውስጥ ሆነ ከውጭ የሚገኝ ምርት በበቂ ሁኔታ እንዲቀርብ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦትን ከፍ ማድረግ። ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ላይ ግሽበቱ የሚታይ ከሆነ በቂ ምርት እንዳይኖር የውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ሊሆን ይችላልና በቂ የውጭ ምንዛሪ በማቅረብ እያስተካከሉ መሄድ። አሁን ያለው አሠራር እየፈጠረ ያለው የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስ የሚቀረፀው ፖሊሲ የውጭ ኩባንያዎችንም በማስገባት እንዲረጋጋ ማድረግንም ይጠይቃል። የውጭ ምንዛሬ ማሻሻያ ስርዓቱም ለዚህ ምቹ ምህዳር ይፈጥራል።

ለዋጋ ግሽበቱ መባባስ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም እንደሀገር ፈተና እየሆኑ ካሉ ችግሮች አንዱ ስግብግብ ነጋዴዎች በአቋራጭ ለማትረፍ የሚያደርጉት ሩጫ ነው። ሰሞኑን መንግስት ይፋ ያደረገውን የማክሮ ኢኮኖሚ መሻሻያን ተከትሎ ከዶላር መጨመር ጋር ተያይዞ በመርካቶና በሌሎች ዋናዋና የገበያ ስፍራዎች የሸቀጦችን ዋጋ ለማናርና በአቋራጭ ለመበልጸግ እየተደረጉ ያሉ ሩጫዎች ማሳያዎች ናቸው።

ይህንኑ ተከትሎ ያለአግባብ የዋጋ ጭማሪ ባደረጉ፤ ምርትን በደበቁና ባከማቹ በአጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ስርዓቱን ተከትሎ የተደረገውን የዶላር ዋጋ ማሻሻያ ምክንያት በማድረግ በአቋራጭ ለመክበር ጥረት ባደረጉ ነጋዴዎች ላይ እርምጃ መውሰዱን አዲስ አበባ ንግድ ቢሮ አስታውቋል። ሆኖም ርምጃው ቀጣይ ሆኖ አላየነውም።

የንግድ ቢሮው እየወሰደ ያለው እርምጃ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ቢሆንም ድርጊቱ ግን አስተዛዛቢ ነው። መንግሥት የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎርም ማድረጉን ባስታወቀበት በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ሸቀጦችን በመደበቅ፤ በማከማቸትና ከልካቸው በላይ ዋጋ በመቆለል የሸቀጦች ዋጋ እንዲጋር እና ኑሮ ውድነቱ እንዲባባስ ለማድረግ ሲሞክሩ ታይተዋል። እነዚህን ስግብግብ ነጋዴዎች ፊር ለማስያዝ የተወሰደው ርምጃ ጥሩ የሚባል ቢሆንም በተቃራኒው የመንግሥት ተቋማት ዋጋ እየጨመሩ የኑሮ ውድነቱ እንዲባባስ መደረጉ ከስግብግብ ነጋዴዎች ያመለጠውን ህዝብ ተመልሶ በሌላ ማነቆ ውስጥ እንዲገባ ያደረገ ነው።

የመንግሥት ተቋማት ኑሮ ማረጋጋት እና ኅብረተሰቡንም ከምዝበራ መታደግ ሲገባቸው ራሳቸው እየተሸቀዳደሙ የዋጋ ጭማሪ ማድረጋቸው ተቋማቱ የተቋቋሙበትን አላማ እንድንመረምር የሚያደርገን ነው። አብዛኞቹ ህዝብን ለማገልገል የተቋቋሙ ቢሆኑም በሂደት የነጋዴ ባህሪ የተላበሱ እና ትኩረታቸው ሁሉ ከኅብረተሰብ እርካታ ይልቅ ትርፍን የሚያሳድዱ ሆነዋል።

በአጠቃላይ በየቀኑ እንደ ሽምጥ ፈረስ የሚወረወረው የኑሮ ውድነት የአብዛኛውን ድሃ ኅብረተሰብ ወገብ እያነበጠና ከባድም የኑሮ ፈተና እየሆነ መምጣቱን አምኖ ለችግሩ ትኩረት መስጠት የመፍትሄው አንድ እርምጃ ሊሆን ይገባል። በተጨባጭም ለኑሮ ውድነቱ ተገቢውን ትኩረት መስጠቱን የሚያረጋግጡ እርምጃዎችን መውሰድ ይጠበቅበታል። ቀጥሎም መንግሥት ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ የአቅርቦት ሥርዓቱን ማስተካከልና ምርታማነትን ማሳደግ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ችግሩን ከስሩ ለመንቀል ያስችላል። ከዚሁ ጎን ለጎን ግን የመንግሥት ተቋማት ቢያንስ በዚህ ወቅት የዋጋ ጭማሪ ከማድረግ ሊቆጠቡ ይገባል።

ስፖርትና መዝናኛ

የዘመን ጥበብ

ሲትኮም

ሲዲያ ተስፋዬ

ሳቅ መፍጠር ምናልባት ለአንዳንድ ሰዎች ቀላል ነገር ሊሆን ይችላል። አንዳንዴ በአካላዊ እንቅስቃሴ ብቻም ሰዎች እንዲስቁ ማድረግ ይቻላል። ቀልድ እና ቁምነገርን በአንድ ላይ ማቅረብ ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው። ይህም ሰዎች በደረቁ ታግሰው የማይሰሙትን፣ መንግሥት እንዲነሳበት የማይሻውን፣ ተቋማት ሊታመቡበት የማይፈልጉትን፣ ማኅበረሰብ ትክክል ነኝ በሚል ካባ ሸፍኖ የሚያሸሞነሙንና እንዲነካበት የማይፈልገውን ጉዳይ እንዲሰሙት አድርጎ በቀልድ አዋዝቶ ማቅረብ እንደማለት ነው። ይህን ማድረግ የቻለ ወይም የሚችለው ሲትኮም የተባለው የተከታታይ ፊልም ዘውግ ነው።

ሲትኮም (Sitcom) "Situation-Comedy" ከሚለው የእንግሊዝኛ ጥምር ቃል የወጣ ነው። 'ከሁኔታዎች ውስጥ ወይም በሁኔታዎች የሚፈጠር አስቂኝ ትዕይንት' የሚለው ሃሳብ ለትርጉም ይቀርበዋል። ለቃሉ ቀጥተኛና አቻ ሀገርኛ ትርጉም የተሰጠው ባይመስልም፤ በኢትዮጵያ የፊልም ዘርፍ ይልቁንም በቴሌቭዥን ተከታታይ ፊልም ዘርፍ ዝነኛ ከሆነ ሰነባብቷል። እንደውም በርካታ ወይም ሁሉም ለማለት በሚቀርብ መጠን የቴሌቭዥን ጣቢያዎች የሲትኮም ቤት ሆነዋል፤ አልፎም የሲትኮም ዘውግ ያላቸው ፊልሞችን ከመሰናዶዎች መካከል አለማካተት የማይቻል አልያም ከልክል የሆነ ይመስላል።

ሲትኮም ከዓለም ጋር እንደ አንድ ዘውግ ተለይቶ የተዋወቀው በሬዲዮን ሥራዎች አማካኝነት እንደሆነ የተለያዩ በትስስር መረብ ጎሰሳ የሚገኙ መዛግብት ያስረዳሉ። ይህም በአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ወደ 1926 የሚመልሰን ነው። በኋላ በዛው የአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር 1946 በእንግሊዝ የመጀመሪያው ሲትኮም ተብሎ የተጠራ ፊልም ለቴሌቭዥን ተመልካቾች ለዕይታ ቀርቧል። በኋላም የተለያዩ ሀገራት የፊልም ኢንዱስትሪዎች ለዘውጉ እውቅና ሰጥተው መሥራት ቀጥለዋል።

በዚህ ዘውግ ዝነኛ ከሆኑት መካከል 'ፍሬንድስ' አንዱ ነው። በጓደኝነት የተጣምሩ፣ በአሜሪካ ኒውዮርክ ከተማ ውስጥ የሚኖሩና እድሜያቸው በሃያዎቹ መጨረሻ አካባቢ የሚገኝ ስድስት ወጣቶችን ታሪክ ያስቃኛል። ይህ ፊልም ከአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር 1994 ጀምሮ እስከ 2004 በዕይታ የቆየ ሲሆን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዝናን ያተረፈ ብሎም በትውልድ መካከል ሳይሰለች አሁን ድረስ የሲትኮም ዘውግ ዳርቻ የሆነ ያህል እየተጠቀሰ የቆየ ነው።

የዚህን ሲትኮም ተወዳጅነት እና ዘመን አይሽሬ ሆኖ መቆየቱን በተመለከተ የተጻፉ ዘገባዎች፣ በፊልሙ የተሳሉ ገጸ ባህርያት የተለያዩና ለአብዛኛው/ለሁሉም የቀረቡ መሆናቸውን እንደ ምክንያት ያነሳሉ። ተመልካቾች ራሳቸውን ወይም ከራሳቸው ማንነት ጋር የሚቀራረብ መልክን በቀላሉ በገጸ ባህርያቱ ውስጥ ማግኘት መቻላቸው ተቀባይነት እንዲያገኝ አድርጎታል የሚሉም አሉ። አዲሱ ትውልድ ደግሞ መለስ ብሎ የቀደመውን ትውልድ መልክ የሚያይበት መሆኑና ያም የቀረበበት ለዛ ማራኪ መሆኑ ዘመን እንዲሻገር አስችሎታል ሲሉ ያነሳሉ።

በዚህ ሲትኮም ላይ ሳቅ የሚፈጥሩ ትዕይንቶችና ንግግሮች ላይ የተመልካቾች የሳቅ ድምጽ (Laugh Track) ይሰማል። ይህም በአብዛኛው አሁን ላይ እንደምናየው የሳቅ ድምጽ ተቀድቶ፣ ቅጂው በየትዕይንቱ የሚለቀቅበት ሳይሆን በቀጥታ ተመልካቾች እየተመለከቱ ግብረ መልስ የሚሰጡበት ነበር። እንደውም የሲትኮሙ ዳይሬክተሮች ሳቅ ያልተፈጠረባቸው ትዕይንቶች ላይ በዛው ማስተካከያ አድርገው ሳቅ እንዲፈጥር ያደርጋሉ።

ይህን በኢትዮጵያ ወጣቶች ዘንድም ተወዳጅ የሆነ ሲትኮም ያነሳነው ለማሳያ ነው። ታዲያ የአንዳንድ ሲትኮሞች መቼት እንደ ፍሬንድስ በመድረክ ግንባታ ታግዞ ታዳሚዎች በቀጥታ በተገኙበት ይቀርባል። እንደዛው ሁሉ በታሪኩና በገጸ ባህርያቱ መልክ መሠረት መቼታቸው ይቀረጻል። ካፌ ውስጥ፣ መኖሪያ ቤት፣ ትምህርት ቤት የመሳሰለው ከመቼቶቹ ይገኙበታል።

"ሲትኮም ማለት አንድ የተወሰነ 'ሁኔታ' ላይ መሠረት የሚያደርግ ነው። ሲትኮሞች አንድ ጉዳይ/ሁኔታ ያነሱና በዛ ላይ ሳቅ የሚፈጥሩ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ተያያዥ ሆነው የሚቀጥሉ ናቸው።" ሲል የሚያስረዳው የኢትዮጵያ ፊልም አጥኚ እና ተመራማሪ ምኒልክ መርዕድ ነው። ምኒልክ አያይዞም እነዚሁ በአንድ ሁኔታ መነሻነት ሳቅን እየፈጠሩ የሚሄዱ አልያም ተያያዥ ታሪክ ይዘው ሳቅን በመፍጠር የሚቀጥሉ ፊልሞች፣ አንዳንዶቹ የሳቅ ድምጽ (Laugh track) እንደሚጠቀሙ አውስቷል። ይህ የሳቅ ድምጽን የማስገባት ጉዳይ ግን አከራካሪ መሆኑን ይጠቅሳል። ያም ሆነ ይህ ሲትኮም ፊልሞች ተወዳጅ ሆነዋል። እንደ ምኒልክ ገለጻ፣ ከቀሪዎቹ ተከታታይ ፊልሞች (Series) ባልተናነሰ በደንብ መታየት ጀምረዋል።

ሲትኮም በኢትዮጵያ በዚህ ጊዜ ተጀመረ ለማለት ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ጉዳይ ሳይሆን አልቀረም። ምክንያቱ ደግሞ የሲትኮም ዘውግ ጠባይ ያላቸው 'ጭውውት' ተብለው በቴሌቭዥን የሚቀርቡ ሥራዎች ነበሩ። በዛው መጠን ከቴሌቭዥን ቀደም ብሎም በሬዲዮም የሚደመጡ ጭውውቶች ይታወቃሉ።

"ሲትኮም የሚል ስም ባይሰጡትም ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ሥራዎች ተሞክረዋል። ቲቪ ላይ በጭውውት መልክ ይቀርቡ የነበሩ የልመንህ፣ አለባቸው እና እንግዳዘር፤ ደረጄ እና ሀብቴ የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ሳቅ/ኮሜዲ ፈጥረው በጭውውት ያቀርባሉ።" ሲል ያብራራል። እነዚህ ጭውውቶች ታዲያ የእረፍት ቀናትን ማድመቂያ፣ የበዓላት ቀን ማሞቂያና መጨዋወቻ፣ አንዳንዴም ማኅበራዊ ሕይወትን በተመለከተ መልዕክቶች የሚተላለፍባቸው ሆነው ይታዩ ነበር። እነዚህ ሲትኮም ውስጥ ይመደባሉ ወይ የሚለውን በቀጥታ መመለስ ባይቻልም፤ የሲትኮም ባህርያት ግን ያሏቸው ናቸው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሲትኮም የሌለበት የቴሌቭዥን ጣቢያ ቢታሰስ ለማግኘት ያዳግታል። ለምን እንዲህ ተበራከተው ታዩ፣ ለምንስ በመደበኛ ፊልሞች ይሳተፉ የነበሩ ባለሞያዎች ሳይቀር በአብዛኛው ተምመው ወደዚሁ ዘውግ እንዲሄዱ ያደረጋቸው ምን ይሆን የሚለው እንደ ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም።

በዚህ ጉዳይ ላይ ምኒልክ ዕይታውን አካፍሏል። ሲትኮም አይነኬ የተባለንና በዝርው ለመናገር የማይደፈርን በቀልድ አዋዝቶ ለማቅረብ ማገዙ ባለሞያዎች እንዲመርጡት፣ ተመልካችም እንዲመለከተው አድርጓል ይላል። "ፖለቲካውን ቀጥታ መናገር አይቻልም፣ ሊያስጠይቅ ይችላል። ሲትኮም ሆኖ ሲመጣ ግን ማንሳት ወይም መንካት ይቻላል።" ሲል ያብራራል።

እዚህ ላይ እንደ ምሳሌ "ምን ልታዘዝ" የተሰኘውን ሲትኮም ማንሳት ይቻላል። በዚህ ሲትኮም ላይ የ'ፖለቲካዊ ሳታየር' ዓይነት ይዘት ከመታየቱ ባለፈ ማኅበረሰብን ጨምሮ 'አንቂ ነን' የሚሉ አካላት ላይ ትችቶች ይቀርቡ ነበር። ከሲትኮሙ በአንዱ ክፍል ላይ 'የሴቶች መብት አቀንቃኝ' (Feminist) የሆኑ ሰዎችን አካሄድ ያሳያል። በካፌው ውስጥ ሻይ እና ቡናን ሳይቀር በሴት አንቀጽ መጠራት አለበት ብለው 'ሲሞግቱ' ያሳያል። በዚህም ሳቅ ፈጥሮ፣ አካሄዱን ይተቻል፤ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ራሳቸውን እንዲያጤኑ ያመላክታል። በተመሳሳይ በሲትኮሙ የ'ምን ልታዘዝ ካፌ' ሥራ አስኪያጅ ጋሽ አያልቅበት እና በአስተናጋጆቹ ብሎም በባሬስታው መካከል ባለው ግንኙነት ውስጥ ፖለቲካዊ ትችቶች ሲሰነዘሩ ይታያል።

"ትችት በሲትኮም መቅረቡ ተአማኒነትን እንዲያገኝ ያስችላል። አንዳንዴ አዲስ የሆነ ነገርን ማኅበረሰቡ እንዲቀበል ለማድረግም ሲትኮምን ይጠማሉ። ሲትኮም ማምለጫ ሊሆን ይችላል። በድምሩ እንዲህ አሁን ላይ ሲትኮም በብዛት የሚታየው በቀልድ ሲመጣ መንግሥት እንዳይጠይቅ፣ ማኅበረሰብም ጥያቄ እንዳያነሳ አድርጎ 'ኮሶን በማር ጠቅልሎ' ዓይነት አቀራረብ ስላለው እንደሆነ አስባለሁ።" ሲል ምኒልክ ዕይታውን አብራርቷል።

ወደፊት የፖለቲካ ዘውግ ሊመጣ ይችላል የሚል ግምቱን ግን ሳይጠቅስ አልቀረም። "በመንግሥት የሚደገፉ የፖለቲካ ቅላጼ ያላቸው ፊልሞች ሊመጡ ይችላሉ የሚል ግምት አለኝ። አሁንም እንደዛ ዓይነት ፊልሞችን እያየን ነው። ከዛ ደግሞ አሁን ያለውን የፖለቲካ አካሄድ የሚቃወም የፊልም ሠሪ ሊነሳ ይችላል።" በማለትም ወደፊቱ ይዞታል ብሎ ያመነውን አመላክቷል።

የፊልም ዳይሬክተር ብርሃኑ ሽብሩ በዘውጉ የሚታየውን አቀራረብ ይተቻል። የሰዎችን ወይም የተመልካችን ፍላጎት ብቻ ይዘው የሚከተሉም አሉ ባይ ነው። አሁን ላይ በዝቶ መታየቱንም በተመለከተ "ወረት ነው፤ ያልፋል" ሲል ያስቀምጣል። ይህንንም ቀደም ብሎ በነበሩ ዓመታት በፊልሞች ርዕስ ላይ ይስተዋል ከነበረው ተመሳሳይ ይዘት ጋር ያነጻጽረዋል።

"አንድ ወቅት ላይ ሲኒማ ቤት የነበሩ ፊልሞች በሙሉ ርዕሳቸው እንግሊዘኛ ነበር። ልክ እንደዛው ወረትና ሽሚያ ስለሆነ ነው። ግን ያልፋል። ቁጭ ብለውም አይነጋገሩም። አንድ ሲትኮም ተወደደ ከተባለና ያም የሆነው ሳቅ ስለፈጠረ እንደሆነ ከታሰበ ሌላውም ቀጥታ ወደዛው ሥራ ይገባል። ሀገር ነክ የሆነ ነገር ቢሠራ ትልቅ ትርጉም ይሰጥ ነበር። ግን ጫጫታና ሳቅ እየሆነ ነው። እያመመን መሳቅ ሆነ። አንዳንዴም በሰው የሚያሸሟጥጡ ነው የሚመስለኝ።" ሲልም ዕይታውን አካፍሏል።

ነገሩን ከወቅታዊ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ አለመረጋጋት ጋር፣ ከሰዎች ሥነ ልቦናዊና አእምሯዊ ሁኔታ ጋር የሚያገናኙት አሉ። ከሰላም ማጣትና በተለያየ መልክ እሳት ላይ ከተጣደው ኑሮ ሰዎችን ለማሳረፍ፣ የብሶትና ችግር መተንፈሻም ነው ብለው የሚያምኑ አሉ። ብርሃኑ በበኩሉ በዚህም እንደማያምን ያስረዳል። "እኔ መተንፈሻ ነው ብዬ አላስብም። አዎን! እንደ ሀገር ጭንቀት አለ፣ ግጭት አለ። በየትኛውም ዘውግ ቢሆን ግን ሥራዬን ሳቀርብ ምን መልዕክት አስተላልፋለሁ ነው እንጂ ላስቅ በሚል አይደለም/መሆንም የለበትም። መናገር የምፈለገው ነገር ወይም ምን እናገራለሁ ነው ጥያቄው። ፖለቲካን ፈርተው አሁን አሁን ዝም ብሎ ማሳቅ ላይ አርፏል። ያንንም ሲትኮም ብለው ይጠሩታል። እሳቤው ከማዕበሉ ጋር ሆኖብን ነው።" ብሏል።

ሁሉም 'ሲትኮም' በሚል ዘውግ የሚጠሩ 'ሲትኮሞች' በተመሳሳይ ጥንቃቄና የባለሞያ ቅኝት የሚሠሩ አይደሉም። ከመብዛታቸው በላይም በጥራት እና በአግባብ የመሠራታቸው ነገርም ወሳኝ ነው። ምኒልክም በዚህ ላይ ሃሳቡን እንዲህ ሲል አካፍሏል።

"ቀልድ ለዛ ይፈልጋል። ለዛ ባለው መልኩ ማቅረብ ያስፈልጋል። አንዳንዴ የዝግጅት ማነስ የሚያመጣው ይመስለኛል። ኮሜዲ የሚባለው ነገር በፊልም ቅርጽ እንዴት መምጣት አለበት የሚለውን በደንብ ባለማሰብ ለዛ ቢስ ሥራ ሊቀርብ ይችላል። ምን እያሉ ነው እስከንል ድረስ አንዳንዴ መስመር መሳት ያጋጥማል።"

ከዚህ በተቃራኒ መቼታቸውን የቤተሰብ ሕይወት ላይ አድርገው የተሠሩትንና ተጨባጭ መልዕክትን ለዛ ባለው ቀልድ እያቀረቡ ነው ያላቸውን ሲትኮሞች እንደማሳያ ያነሳል። ለምሳሌ 'በስንቱ' የተሰኘው ሲትኮም አንደኛው ነው። ይህ በኢቢኤስ ቴሌቭዥን የሚቀርብ ሲትኮም፣ ማኅበራዊ ሕይወትን በደንብ ይተቻል፤ በተለይ በስንቱ በተባለው ገጽ ባህሪ በኩል። በዚህ ሲትኮም ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዴት ነው የሚያዩት፣ ሚስቶችስ የሚለው ይታያል። ከሰፊው ቤተሰብ (አማት እና አማችን ጨምሮ) ጋር ያለው መስተጋብር ምንድን ነው የሚለውንም በሚገባ ለማየት ይሞክራል። ሰውም/ተመልካቹም እንዴት እናት እና አባት በልጅ መካከል እንዲህ ያለ መስተጋብር ሊኖር ይችላል ብሎ ሊጠይቃቸው ይችላል።

እንዲህ ባለ ዕይታ የሚሠራ ሲትኮም ውስጥ በማኅበሰረቡ እና በፊልም ሠሪው መካከል ቅብብል ይኖራል። ማለትም ፊልም ሠሪዎች ማኅበረሰቡን ሲመረምሩና ሲተቹት፣ አንዳንዴ ማኅበረሰቡም በበኩሉ በደንብ አልተወከልንም ሲል ጥያቄ ያቀርብባቸዋል። ሲትኮም በዚህ ረገድ፣ በተሠራበት ጥንቃቄ መጠን በድምሩ መስተካከል ያለበትን አካል ሂስ ለማድረግ ምቹ ነው።

የሲትኮሞች በብዛት መቅረብ ጥራት ላይ ጥርጣሬን ከመጫሩ በቀር፤ በቀረፃ፣ በታሪክ አወቃቀር፣ በገፀ ባህርያት ግንባታና በአቀራረብ ለየት ብለው ለመምጣት የሞከሩም አሉ። ከእነዚህም በባላገሩ ቴሌቭዥን ይታይ የነበረው 'ሦስት ሁለት አንድ' የተሰኘ ሲትኮም እና በቅርቡ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን መታየት ላይ የነበረው 'ግራ ቀኝ' ተጠቃሽ ናቸው። በስንቱ፣ አስኳላ፣ ምን ልታዘዝ፣ ቤቶች፣ ዘጠነኛው ሺህ፣ ሲስተርሊ ብራዘርሊ፣ ጎረቤታሞቹ ወዘተ በዕይታ ላይ ካሉና ቀደም ብለው ከቀረቡት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

ርግጥ ነው! ዘውጉ በበርካታ ጠባዮቹ የተነሳ አሁን ላይ ተመራጭ ዘውግ እየሆነ መጥቷል። ተመልካችና ጊዜም ተባብረው እያነጠሩ በጥሩ ሁኔታ የተሠሩትን ተፅዕኖ ፈጣሪ እና ዘመን ተሻጋሪ ያደርጓቸዋል።

ማህበራዊ

ልዩ ልዩ

“ክብርና ፍቅር ለአረጋውያን!”

ቤዛ እሸቱ

ጸጉራቸው ገብስማ፤ እድሜያቸው ቢገፋም ፈርጠም ያለ ትክለ ሰውነት የታደሉና ፈገግታ ከፊታቸው የማይጠፋ የ75 ዓመት አረጋዊ ናቸው። ጋሽ ሥዩም (ሥማቸው የተቀየረ) የእድሜያቸው ከጎልማሳነት ወደ አረጋዊነት መሻገሩን ተከትሎ የጆሯቸው የመስማት አቅም ተዳክማል። በዚህም ምክንያት ከስንት አንዴ ከሚያገኟቸው ጎብኚዎች ጋር የሚያደርጉት ቆይታ ባጭሩ እንዲቀጭ እያስገደዳቸው ይገኛል። በንግግር መሀል በተደጋጋሚ ምን አልክ/አልሽን? ተቋቁሞ ጨዋታን መቀጠል ለአብዛኞቹ ጠያቂዎቻቸው አድካሚ ስለሚሆንባቸው ከእሳቸው ጋር የሚያደርጉት ንግግር አጭር ነው።

ጋሽ ሥዩም ያኔ ትምህርት እንዲህ ሳይስፋፋ በፊት በእኩዮቻቸው «ቀለሜ» በሚል ቅጽል የሚጠሩ ጎበዝ ተማሪ ነበሩ። በጥሩ ውጤት ትምህርታቸውን ካጠናቀቁም በኋላ ከባለሙያነት አንስቶ እስከ ከፍተኛ ኃላፊነት በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ተዘዋውረው አገልግለዋል። የሚያገኙት የጡረታ ገንዘብ በአንዴ ተከታትለው ለመጡባቸው ደም ግፊት፣ ስኳርና መሰል ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መድሃኒት መግዣነት የሚተርፍ አልሆነም። በጉብዝና ዘመናቸው ለፍተው ያሳደጓቸው አራት ልጆች ግን ደርሰው ዛሬን እየጦሯቸው ነው። ያም ቢሆን ሦስቱ ልጆቻቸው ትዳር ይዘው ከቤት ከወጡ ቆይተዋል። በዚህ የተነሳ ግፋ ቢል በወር አንዴ ቢገናኙ ነው። እቤት የቀረችው የመጨረሻ ልጃቸውና ባለቤታቸውም ማለዳ ወደ ሥራ ወጥተው ጀንበር ስትጠልቅ ይመለሳሉ። በሥራ ቦታ የዕለቱ ከበርካታ ሰዎች ጋር መዋል የለመዱት ጋሽ ሥዩም አሁን ላይ ብቻቸውን ሙሉ ጊቢ ውስጥ ለመዋል ከተገደዱ ከርመዋል። ለብቻቸው ወጣ ማለት የሚያምራቸው ቢሆንም “ተው አትችልም” የሚለው የባለቤታቸውና የልጃቸው የስስት ቁጣ ሃሳባቸውን ያስቀይራቸዋል። የድሮ የልብ ወዳጆቻቸው በብዛት በሕይወት የሉም፤ ካሉት ጋርም እንደልብ እንዳይገናኙ አድራሻቸው ተራርቆ በእነሱ አቅም መገናኘት ፈታኝ ሆኖባቸዋል።

ስለዚህ የቀኑ አብዛኛው ጊዜ ቴሌቪዥን በማየትና በመተኛት ያሳልፋሉ። ማታ ባለቤታቸውና ልጃቸው ሲመጡ ለጨዋታ ጓጉተው ቢጠብቁም እነሱ በሥራ ዝለው ይመጣሉና ጋሽ ሥዩም ቀን የዋለው ብቸኝነታቸው ማታም ይቀጥላል። ይሄ በሀገራችን የበርካታ አረጋውያን የኑሮ እውነታ ነው። ጋሽ ሥዩም የጤናቸው ሁኔታ እንደልባቸው ባያንቀሳቅሳቸውም ሰው ባገኙ ቁጥር ደስታቸው ወደር የለውም፣ ከእንጀራ በላይ የናፈቃቸው ሳቅ ጨዋታ ነውና ባገኙት አቅም ማህበራዊ ሕይወት ላይ ለመሳተፍም አይቦዝኑም።

ሰው የለመደ ሰው ብቻውን ሲውል ድብርቱን መቋቋም አይችልምና፤ ጋሽ ሥዩምም ብቸኝነት የሌላቸውን ጸባይ እንዲያወጡ እያስገደዳቸው ነው። ከዚህ የባሰው ደግሞ በሀገራችን በተለያዩ የሙያ መስክ ፊት አውራሪ የነበሩ ጀግኖችን መንገድ ላይ እጃቸውን ለልመና ዘርግተው ማየት የተለማመድነው የዕለት ውሎአችን ሆኗል። በዓለም አቀፍ ደረጀ ለ34ተኛ በሀገራችን ደግሞ ለ33ተኛ ጊዜ “ክብርና ፍቅር ለአረጋውያን!” በሚል መሪ ቃል መስከረም 21 ቀን 2017ዓ.ም በጋምቤላ ከተማ የአረጋውያን ቀን ተከብሯል። በበዓሉ ላይ ንግግር ያደረጉት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር የማህበራዊ ዘርፍ አማካሪ አቶ ጌታቸው በዳኔ፣ አረጋውያን በእድሜ ዘመናቸው ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን ለልማት ያዋሉ የሀገር ባለውለታ በመሆናቸው በእርጅና ዘመናቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንዲሁም የጤናና ሥነ-ልቦናዊ ችግር በሚያጋጥማቸው ወቅት ተገቢውን ድጋፍና እንክብካቤ በማድረግ ሁሉም የዜግነት ግዴታውን ሊወጣ እንደሚገባ አፅዕኖት ለመስጠት በዓሉ እንደሚከበር ጠቁመዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መረጃ እ.አ.አ በ2019 በዓለም ላይ እድሜያቸው ከ65 በላይ የሆኑ አረጋውያን ቁጥር 703 ሚልዮን መሆኑን ያሳያል። በኤስያ የሚገኙ አብዛኛው ሀገራት አሁንም እንደድሮ አረጋውያኖቻቸውን ከቤተሰብ ጋር ቀላቅለው በክብር ይዘው ቀጥለዋል። ምእራባውያን በግል ከኑሮ ሩጫ ጋር የቤተሰባቸው አካል የሆኑ አረጋውያንን መንከባከብ ሳይችሉ ሲቀሩ በጋራ ከእኩዮቻቸው ጋር ጊዜ የሚያሳልፉበትን የአረጋውያን ማእከላት በስፋት ገንብተዋል። በእነዚህ ማእከላት የቤተሰብ ፍቅርን ባይተካም በባለሙያ የተደገፈ ተገቢ እንክብካቤና ከእኩዮቻቸው ጋር የመገናኘት አጋጣሚ ተመቻችቶላቸዋል።

እኛም ጋር መቄዶንያ፣ ክብር አረጋውያንና ሌሎች በጣት የሚቆጠሩ ግብረሰናይ ድርጅቶች ከክፍያ ነጻ ዘመድ የሌላቸውን አረጋውያን በመሰብሰብ ምርቃታቸው ለሀገር የሚተርፍበት ሁኔታን ፈጥረዋል። የተወሰኑ የግል ተቋማት በክፍያ የአረጋውያን እንክብካቤ የሚሰጡም አሉ። ሆኖም በርካታ አረጋውያን በጎዳና ሀገር ያቀና እጃቸውን ለልመና ዘርግተው በማረፊያ እድሜያቸው የሰው ፊት የሚያዩበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም። በርካቶች ምን ይሉኝን ፈርተው አደባባይ ባይወጡም ባዘነበለ ጎጇቸው “ምን እበላ?” ብለው ጭንቅ የሆነባቸውና የሀገር ባለውለታዎች ተገቢውን ክብር አላገኙም።

እንደ አቶ ጌታቸው ማብራሪያ፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የአረጋውያንን ጉዳይ የሚከታተልና የሚያስተባብር ክፍል በመሪ ሥራ አስፈጻሚ ደረጃ በማደራጀት መዋቅሩን እስከታች ለመዘርጋት ከሚያደርገው ጥረት ጎን ለጎን የአሠራር ማዕቀፎችን የመቅረጽና የአስፈጻሚ አካላትን አቅም የማጎልበት ሥራ በትኩረት እየሠራ ይገኛል። በቀጣይም የአረጋውያን መብቶች በአግባቡ እንዲታወቁና እንዲከበሩ የአድቮኬሲና የንቅናቄ ሥራዎችን ከመሥራት ባሻገር የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት ተደራሽነትን በማስፋፋት፣ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበርና ሀብት በማሰባሰብ ለማህበራዊና አኮኖሚያዊ ችግር የተጋለጡትን ለመደገፍ የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ ይቀጥላል።

እንደ ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መረጃ ከሆነ በሁሉም የዓለም ክፍል የአረጋውያን ቁጥር በመጨመር ላይ ይገኛል። እ.ኤ.አ እስከ 2050 ባለው ጊዜ በዓለም ላይ የሚገኙ አረጋውያን ቁጥር ከዕጥፍ በላይ በመጨመር አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል። የሀገራችንም ሁኔታ ከዚህ እውነታ የተለየ አይደለም። ዛሬ ላሉን አረጋውያን ተገቢውን ክብርና አስፈላጊውን ድጋፍ ባንሰጥም ቁጥራቸው እየጨመረ ይሄዳል። የዛሬ አምራች ኃይል የነገ አረጋዊ ሲሆን የገቢ ምንጩ፣ የጤናውና የአካላዊ ሁኔታው እየደከመ መሄዱ አይቀርምና ዛሬ ላይ ለአረጋውያን ተገቢ ድጋፍ የሚሰጥበትን ሁኔታ ቆም ብሎ ማሰብ የሁሉም ኃላፊነት መሆኑ ሊዘነጋ አይገባውም።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጃ አረጋውያንን የሚንከባከቡ ሰዎች አረጋውያን ላይ ስሜታዊ የመሆን፤ ስህተቶች ሲያዩ አብዝቶ መተቸት፣ በሌሎች ጉዳይ አላስፈላጊ አስተያየት መስጠት እና ያንንም በሰዎች ፊት በተደጋጋሚ ማንጸባረቅ፣ ብስጩ መሆንና በተለያዩ ምክንያቶች ለተለያዩ ጉዳዮች እምቢ የማለት ባህሪያት ሊያስተውሉ እንደሚችሉ ይጠቅሳል። ሆኖም ከላይ የተጠቀሱት ባህሪያት ሲከሰቱ ከመናደድ ይልቅ በቤት ውስጥ ችግር አለመኖሩን በቅድሚያ እርግጠኛ መሆን የሚገባ ሲሆን፤ ነገሩን በእርጋታ እና በትዕግስት መያዝ፣ እጋውያኑ የሚወዱትን ነገር ማድረግ፣ ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ እና እንዲደመጡ ማድረግ፣ መንፈስን የሚያረጋጉ እና ውስጣዊ ሰላምን የሚሰጡ የሚወዷቸውን ነገሮችን መከወን፣ የሚጠሉትን ነገር በፊታቸው አለማድረግ እንዲሁም ከአቻዎቻቸውና ከሌሎች ሰዎች ጋር ጊዜ እንዲኖራቸው ማድረግ በመፍትሔነት ተጠቅሰዋል። ይሄን ማድረግ ሲቻል በጧሪዎቻቸው ተደስተው የሚመርቁ አረጋውያንን ቁጥር ይጨምራል።

ዓለም አቀፍ

በጂቡቲ ሁለት ጀልባዎች ተገልብጠው 45 ሰዎች ሲሞቱ 61 ደግሞ መጥፋታቸው ተገለጸ

ከጂቡቲ የባሕር ዳርቻ አቅራቢ ሁለት የስደተኞች ጀልባዎች ተገልብጠው ቢያንስ 45 ሰዎች መሞታቸው ሲረጋገጥ 61 ሰዎች ደግሞ የደረሱበት ባለመታወቁ ፍለጋ እየተካሄደ መሆኑን ባለሥልጣናት ገለጹ።310 ሰዎችን ይዘው ከየመን የተነሱት ሁለቱ ጀልባዎች በአፍሪካ ቀንዲ ሀገር ጂቡቲ አቅራቢያ ባለው ቀይ ባሕር ላይ ተገልብጠው አደጋው መድረሱን የመንግሥታቱ ድርጅት የስደተኞች ተቋም (አይኦኤም) አረጋግጧል።

የጂቡቲ የባሕር ጠረፍ ጥበቃ አባላት “እስካሁን ባለን መረጃ መሠረት 61 ሰዎች የገቡበት አልታወቀም። ሰዎቹን ለማግኘት የምናደርገው ፍለጋ ተጠናክሮ ይቀጥላል” ብለዋል። በዓለማችን በርካታ ስደተኞች በሕገወጥ መንገድ የሚጓዝባቸው ናቸው ከሚባሉ አስፊሪ የባሕር መተላለፊያዎች አንዱ የሆነው ይህ ሥፍራ በርካታ አፍሪካውያን ስደተኞች አህጉሪቱን ጥለው ለመውጣት ይጠቀሙበታል።

ከሰኞ ጠዋት ጀምሮ በአደጋው ደብዛቸው የጠፋውን ሰዎች ለማግኘት “መጠነ-ሰፊ ፍለጋ” እየተደረገ መሆኑን ያሳወቀው የጂቡቲ ባሕር ጠረፍ ጥበቃ፣ ከአይኦኤም ጋር በመተባበር እስካሁን 115 ሰዎችን ማዳን መቻሉን ገልጿል። የባሕር ጠረፍ ጥበቃው አከሎ እንዳስታወቀው ጀልባዎቹ ተገልብጠው የሰመጡት ሰሜን ምዕራብ ጂቡቲ ከምትገኘው ዞር አንጋር ግዛት 150 ሜትር ርቀት ላይ ነው።

በየዓመቱ በሺዎች የሚቆጠሩ አፍሪካውያን ስደተኞች ቀይ ባሕርን ተጠቅመው በነዳጅ ሀብት ወደ በለፀጉ የባሕረ ሰላጤ ሀገራት ይጓዛሉ። ስደተኞቹ በሀገሮቻቸው ያሉ ግጭቶችን፣ ተፈጥሮ አደጋዎችን እና የኑሮ ውድነትን በመሸሽ ነው የሚሰደዱት።

ባለፈው ዓመት ሰኔ በተመሳሳይ የመን ድንበር አቅራቢያ ቀይ ባሕር ላይ አንዲት ጀልባ ተገልብጣ 56 ሰዎች መሞታቸውን 140 ሰዎች መጥፋታቸው ይታወሳል። የአደጋው ሰለባ የነበሩት ስደተኞች ከኢትዮጵያ እና ከሶማሊያ የመጡ ነበሩ። ከሟቾቹ መካከል 31 ሴቶች እና ስድስት ሕፃናት ይገኙበታል።

ቀይ ባሕርን ተጠቅመው ከአፍሪካ ቀንድ ወደ የመን የሚጓዙ ስደተኞች ቁጥር በአውሮፓውያኑ 2022 ከነበረው 73 ሺህ ወደ 97 ሺህ 200 ማደጉን አይኦኤም አስታውቋል። አብዛኞቹ ስደተኞች በሕገ ወጥ የሰው አዘዋዋሪዎች አማካይነት ነው ይህን ባሕር መስመር ለማቋረጥ የሚሞክሩት። ስደተኞቹ ብዙውን ጊዜ ለአደጋ የሚጋለጡት በአነስተኛ ጀልባ በከፍተኛ ቁጥር ታጭቀው በአደገኛው ባሕር ላይ ለመጓዝ ሲሞክሩ መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።

እስራኤል እና ሄዝቦላህ ሊባኖስ ውስጥ የፊት ለፊት ውጊያ መግጠማቸውን አስታወቁ

የእስራኤል ጦር በደቡባዊ ሊባኖስ ከሄዝቦላህ ታጣቂዎች ጋር “በቅርብ ርቀት እየተዋጋ” መሆኑን አስታወቀ። ሄዝቦላህ በበኩሉ ወደ ሊባኖስ ድንበር “ሰርገው ከገቡ” የእስራኤል ወታደሮች ጋር ውጊያ መግጠሙን አረጋግጧል። የሊባኖስ ጦር እስራኤል የሁለቱን ሀገራት ድንበር አልፋ መግባቷን ገልጿል።

ጦሩ በመግለጫው ላይ እስራኤል ብሉ ላይን ተብሎ የሚታወቀውን እና የተባበሩት መንግሥታት ቅኝት ሚያደርግበትን የጎላን ተራሮችን ከሊባኖስ የሚለየውን አካባቢ አልፋ በደቡባዊ ሊባኖስ 400 ሜትሮችን ዘልቃ መግባቷን ተናግሯል። የእስራኤል መከላከያ ኃይል በመግለጫው በደቡባዊ ሊባኖስ “በበርካታ አካባቢዎች” ውጊያዎች እየተካሄዱ መሆናቸውን ገልጿል።

የእስራኤል የምድር ጦር ከአየር ኃይሉ ጋር በጥምረት በመሆን “ሽብርተኞችን እንዲሁም የሽብርተኞች መሠረተ ልማቶችን” አውድመዋል ብሏል። በዚህም “ከ150 በላይ መሠረተ ልማቶች” በአየር ጥቃቱ መውደማቸውን ገልጿል። ሄዝቦላህ በበኩሉ ወደ ሊባኖስ ከተማ ማሮን አል ራስ ሰርገው ከገቡ የእስራኤል ወታደሮች ጋር ውጊያ መግጠሙን ተናግሯል።

ከተማዋ ከእስራኤል እና ከሊባኖስ ድንበር 2 ኪሎ ሜትር ብቻ የምትርቅ ናት። እንደ ሄዝቦላህ መግለጫ ከሆነ የእስራኤል ወታደሮች በምሥራቃዊ የሀገሪቱ ክፍል በኩል የገቡ ሲሆን፣ የሚደረገው ውጊያ ቀጥሏል። ሄዝቦላህ ከዚህ ቀደም ወደ ሊባኖስ ሊገባ ያለውን የእስራኤል እግረኛ ጦር እንዲመለስ ማድረጉን ጠቅሶ ነበር።

የሊባኖስ ብሔራዊ የዜና ወኪል ኤንኤንኤ በበኩሉ ሀገሪቱ ከእስራኤል ጋር በምትዋሰንበት ድንበር አቅራቢያ በምትገኝ ደበል የተሰኘች መንደር ላይ ትናንት ረቡዕ ጠዋት በተፈጸመ የአየር ጥቃት ሦስት ሰዎች መሞታቸውን ገልጿል።

ጦሩ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ባሰፈረው መግለጫ ላይ የእስራኤል ጦር የሊባኖስን ድንበር አልፎ 400 ሜትር ያህል ከዘለቀ በኋላ “ከጥቂት ቆይታ በኋላ ተመልሶ ወጥቷል” ማለቱን ቢቢሲ ዘግቧል።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

ነፃ ሃሳብ

በመስከረም የሚደምቁ ኢትዮጵያዊ እሴቶች

መስከረም፤ የአዲስ ዓመት ማብሰሪያ ነው:: በዚህ ወር እንደ ሁልጊዜው ሁሉ ኢትዮጵያውያን ይደምቃሉ:: የኢትዮጵያን ውበት፣ እሴት፣ ባሕል፣ አንድነት እንዲሁም ዘመናትን የተሻገረ ጥልቅ ሰብዓና ለመረዳት የሚሻ ማንኛውም ባእድ በዚህ ወር ብቅ ቢል እልፍ እውቀትን ይገበያል

ሰው መሆን

ብሩህ ወር ነው። ኢትዮጵያውያን ከጫፍ እስከ ጫፍ የሚደምቁበት። በእነዚህ ጊዜያት የኢትዮጵያም የኢትዮጵያውያንም ውበት ጎልቶ ይወጣል። መልከዓ ምደሩ በአረንጓዴ ይሸፈናል። ተራሮች የአደይ አበባ ተክሊል ይጎናፀፋሉ። ቢጫ ቀለም የተስፋ ምልክት እንደመሆኑ መጠን ለመፃኢው ጊዜ ኢትዮጵያውያን በጎውን የሚያልሙበት፣ የተሻለ ለማደግ፣ ይበልጡኑ አንድነታቸውን ለማጠንከር ቃልኪዳን የሚገቡበትን ተስፋን የሚቋጥሩበት ነው።

መስከረም፤ የአዲስ ዓመት ማብሰሪያ ነው። በዚህ ወር እንደ ሁልጊዜው ሁሉ ኢትዮጵያውያን ይደምቃሉ። የኢትዮጵያን ውበት፣ እሴት፣ ባሕል፣ አንድነት እንዲሁም ዘመናትን የተሻገረ ጥልቅ ሰብዓና ለመረዳት የሚሻ ማንኛውም ባእድ በዚህ ወር ብቅ ቢል እልፍ እውቀትን ይገበያል።

ወቅት ከማህበረሰብ እሴት ጋር ምን ያህል ዝምድና እንደሚኖረው ይመለከታል። ባሕል እምነት፣ የማህበረሰብ ስብጥር በአንድና በአንድነት እንደ ጅረት ኩልል ብለው ሲፈሱ ይመለከታል። እነዚህ እሴቶች በኢትዮጵያ አንጂ በሌላ በማንኛውም ቦታ ማግኘት አይቻልም።

በመስከረም ወር መልከዓ ምድሩ ብቻ አይደለም በለምለም የሚሞላው የኢትዮጵያ ገበያዎች፣ አደባባዮች ይደምቃሉ። የገበያው ግርግር እንኳን ለዜጋው ለባእድም ቢሆን አንዳች በጎ ስሜትን የሚያጋባ ነው። ከጥንት ጀምሮ ሀገረ መንግሥት የመገንባት ቀዳሚ የሆነችው ኢትዮጵያ ሕዝቦቿ እንዴትና በምን መንገድ ህብረታቸውን ጠብቀው ዛሬ ድረስ መዝለቅ እንደቻሉ የመስከረም ወር ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። በየገበያው የሚታየው የቋንቋ ስብጥር፣ የሃይማኖት ብዝሀነት፣ የባሕል ህብር ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ ያደረጋት ምን እንደሆነ ያሳብቃሉ። ለዚህ ነው ከሌላው ጊዜ በተለየ መስከረም ለኢትዮጵያውያን ልዩ ትርጉም የሚኖረው።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ ፖለቲካ የሃሳብ ልዩነት፣ ፖለቲከኞችና ግላዊ መሻታቸው አንድነታቸውንና ከጥንት የነበረ ወዳጅነታቸውን በቀላሉ የሚሸረሽር አይደለም። ለዚህ ማሳያ የምናደርገው አሁንም የመስከረም ወርን ነው። በዚህ ወር ኢትዮጵያውያን በጎዳናዎች ላይ ሕዝቦች ባሕል፣ ሃይማኖት ሀገር በቀል እውቀታቸውን አውቀው የሚወጡበት፣ የህብረ ብሔራዊ እሳቤያቸው በተግባር የሚገልጡበት ነው።

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች በመስቀል በዓል በኢትዮጵያ አደባባዮች ላይ ሃይማኖታዊ እሴቶቻቸውን ሲያንፀባርቁ፣ በሌላ መልኩ ባሕላዊ ትርጉሙ ከፍ ያለው ኢሬቻም በተመሳሳይ ይከወናል። በእነዚህ በዓላት ወቅት የኢትዮጵያውያን አንድነትና መተባበር ይበልጡኑ ጎልቶ ይታያል። ከልዩ ልዩ የዓለማችን ክፍሎች የኢትዮጵያውያን ብቻ የሆነው ባሕላዊ፣ ሃይማኖታዊ እሴቶች ለመመልከትና በጋራ ለማክበር ይታደማሉ።

በመስከረም ወቅት የውጭ ሀገር ጎብኚዎች ብቻ አይደሉም ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት፤ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጭምር ወደናፈቁት ሀገራቸው በከፍተኛ ጉጉትና የናፍቆት ስሜት ይገባሉ። እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ተራርቀው የነበሩ ዘመድ፤ ወዳጅ፣ ቤተሰብም ይጠያየቃሉ።

ደቡብ የነበረው ወደ ምስራቅ፤ ምዕራብ የነበረው ወደ ሰሜን ጉዞ ያደርጋል፤ የተነፋፈቀ ይገናኛል። ተማሪዎች እውቀትን ለመገበየት የሚናፍቁበት ወር ነው፤ ወርሀ መስከረም። በመስከረም ሰው ብቻ ሳይሆን የቤት እንስሳቱ ይጠግባሉ፤ ከብቶች ለግጦሽ በተዘጋጀ ሜዳ ላይ ይቦርቃሉ። ምን አለፋችሁ መስከረም ለመላው ኢትዮጵያውያን የአዲስ ተስፋ፣ የአዲስ እሳቤ፤ የአዲስ ዓመት ነው።

ለዚህ ነው መስከረም እኔ በዚህ ላይ የጠቀስኩትም ሆነ ያላነሳኋቸውን አያሌ ሀብቶች እንደመያዙ መጠን አንድነታችንን ከነበረው በተሻለ የምናጠናክርበት፤ ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ ላይ በበጎ ገፅታ እንድትነሳ የምንሰራበት፣ ቱሪዝም የሚያድግበት፣ ባሕል፣ ወግ፣ ሀገር በቀል እውቀታችን ለዓለም ሕዝብ ገልጠን የምናስተዋውቅበትና ኢኮኖሚያዊ አቅማችንን የምናፈረጥምበት ልዩ ወር አድርገን ልንወስደው ይገባል። ከሁሉም በላይ ህብረታችን፣ አንድነታችንና ውብ ማንነቶቻችን አብረን ለመኖር መሰረት እንደሆኑን ሁሉ በቱሪዝምም ከዓለም ቀዳሚ የሆነ መዳረሻ እንድንሆን መሥራት የሚገባን።

በዓለማችን በቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ እመርታን ያሳዩ ሀገራት ቁልፍ ሚስጢር ያላቸውን ሀብት አከብረው፣ ጠብቀው፣ አልምተውና አስተዋውቀው መሸጥ ስለቻሉ ዛሬ የደረሱበት የእድገት ደረጃ ላይ ይገኛሉ። እኛ ኢትዮጵያውያንም ከዚህ ትምህርት ልንወስድ ይገባል። ብዝሀ ሀብታችን፣ እና ብዝሀነታችን አንድነታችንን ከማጠናከር የተሻገረ ታላቅ የኢኮኖሚ አቅም መፍጠሪያ መሆኑን አውቀን ሳይውል ሳያድር ወደ አቅም ልንቀይረው ይገባል። በእጅ የያዙት ወር አንደሚባለው ዓይነት ብሂል የያዝነው ሀብት የሸማችን ማቅለያ እንጂ እራሱ ሸክም ሊሆንብን አይገባም።

በመስከረም ወቅት ያሉትን ባሕላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶችን ወደ ቱሪዝም መስህብነት ቀይሮ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የሚያስችል አቅም መፍጠር ያስፈልጋል። ያሉት መስህቦች ብዛት መልካም አጋጣሚ ቢሆንም ቱሪዝም ዘርፉ ይህንን ወደ አቅም ለመቀየር የሚያስችል ትክሻ መፍጠር ይኖርበታል። በተለይ በመሠረተ ልማት፣ በትራንስፖርት፣ በአገልግሎት ዘርፍ፣ በሰለጠነ የሰው ኃይል፣ አሰራርን ከማዘመን አንፃር ከመንግሥት ተቋማት ጀምሮ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የራሱን ድርሻ መውሰድ ይጠበቅበታል።

ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ጎብኚዎች በአንድ ቦታና ሁነት ላይ ብቻ እንዳያተኩሩ ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ካሉ እሴቶች እውቀትና ልምድን ይዘው እንዲመለሱ ማድረግ ያስፈልጋል። እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ክፍል ተወዳጅ፣ ማራኪና ለጎብኚዎች አዝናኝ ቆይታን እንዲያገኙ ማድረግ የሚያስችል አቅም ያለው ነው። በተለይ በመስከረም ወር ከደቡብ እስከ ሰሜን፣ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ ያለው የሀገሪቱ ክፍል ባሕላዊ እሴቶቹ ጎልተው የሚታዩበት ነው። በመሆኑም ጎብኚዎችን ወደ ሁሉም አካባቢዎች ጉዞ አንዲያደርጉ በማመቻቸት የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት ማሳደግ ይገባል።

በመስከረም ወቅት የአደባባይ በዓላት ላይ ለመታደም ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ጎብኚዎች በርካታ ናቸው። ይሁን እንጂ ይሄ ብቻ በቂ አይደለም። ከዚህም በላይ ጎብኚ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባና ልዩና ውብ የሆኑት ኢትዮጵያዊ እሴቶቻችን እንዲተዋወቁ ማድረግ ያስፈልጋል። ጎብኚዎችም ስለ ክብረ በዓሎቹ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ሲሄዱ በበጎ መልኩ እንዲያስተዋውቁ ማድረግ ያስፈልጋል። ጎብኚዎች ስለ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ በዓሎቹ ምንነትና ትርጓሜም ትክክለኛው መረጃ እንዲኖራቸው በበዓሉ ወቅትም ሆኖ ከዚያ ቀደም ብሎ ማስገንዘብ የሁላችንም ድርሻ ነው። ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያዊነት በእነዚህ እሴቶች የሚደምቅና የሚገለፅ እንደሆነ በተግባር የምናሳይበት ዕድል መፍጠር አለብን።

ይህ ብቻ አይደለም የአደባባይ በዓሎቹ የቱሪስቱን ቆይታ ሊያረዝም በሚችል አግባብ በትክክል ሊተዋወቁ ይገባል። በተጨማሪ ከፍተኛ ቱሪስት በሚገኝበት በዚህ ወቅት ከዚህ ቀደም ምንም ያልተዋወቁ አዳዲስ መስህቦችን አጋጣሚውን ተጠቅሞ ለጎብኚዎቹ የማስተዋወቅ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። ለምሳሌ ያህል የሸዋል ኢድ በዓል፣ የድሬ ሼክ ሁሴን፣ በደቡብ ኢትዮጵያ የሚከበሩ የአዲስ ዓመት በዓላትና ሌሎች የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ መስህቦችን ማስተዋወቅ ይገባል።

ኢትዮጵያ የብዝሀ እሴቶች መገኛ፤ የማህበረሰብ ጥልቅ እውቀት መፍለቂያ መሆኗን ስንናገር በተግባር በሚገለፅ መልኩ መሆን አለበት። እውቀት፣ የተፈጥሮ ፀጋ፣ ቀደምት ታሪክ፣ ጥንታዊ ስልጣኔ፣ የሰው ዘር መገኛ እንዲሁም የሰው ልጆች የሥልጣኔ መነሻ መሆናችንን በማያሻሙ ማስረጃዎች ማስቀመጥ ይጠበቅብናል። እዚህ ጋር ጥቃቅን ነገሮች ጥቅሉን ገፅታችንን እንዲያበላሹብን ልንፈቅድ አይገባም።

ኢትዮጵያ «ውብ ሀገር፣ እሴት፣ ሀገር በቀል እውቀት፣ የማህበረሰብ ስብጥር» እንዳላት እየተናገርን በዚያኛው ጎን ደግሞ እነዚህን አውነታዎች የሚያደበዝዙ፣ ገፅታን የሚያጠለሹ ጉዳዮችን ችላ ልንላቸው አይገባም። ለዚህ ነው የሁሉ ነገር መጀመሪያ በሆነው የመስከረም ወር አሉታዊ ጎናችንን ልናከም የሚገባን። ከእነዚህ መካከል ሰላም ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል።

የሕዝቦችን አንድነት የሚሸረሽር እኛነታችንንና ያሉንን መስህቦች ለመመልከት የሚመጡ ቱሪስቶችን ደህንነት ስጋት ላይ የሚጥል እዚህም እዚያም የሚታይ አለመረጋጋት ተገቢውን እልባት ልንሰጠው ይገባል። ለዚህ ደግሞ መፍትሔው አይርቀንም። ሀገር በቀል እውቀት የሽምግልና ሥርዓት በእጃችን ነው። ግጭትን ከስር መሰረቱ በብልሃት መፍታት የሚያስችል እሴቶች አሉን። እነዚህ ሀብቶች አይደለም የራሳችንን ችግሮች አልፈው የጎረቤት ውስብስብና ጥልፍልፎችን መፍታት ይችላሉ።

ደጋግሜ እንዳነሳሁት መስከረም ለኢትዮጵያም ሆነ ለኢትዮጵያውያን አያሌ በረከቶችን የያዘ ልዩ ወር ነው። በፍቅር፣ ብሩህ በሆነ ተስፋ የጀመርነው የመስከረም ወር ለዘላቂ ህብረት፣ ቀጣይነት ላለው አንድነት፣ ለፈጣን እድገትና ኢትዮጵያውያን የሚኮሩበት ማንነት የምናረጋግጥበት ሊሆን ይገባል። ከሁሉም በላይ ህብረታችን ጠላቶቻችንን ሊያስደነብር፤ ፍቅርና አንድነታችን ደግሞ በጎ ለሚያስቡልን ደስታን የሚፈጥር፣ እድገትና ዘመናዊት ኢትዮጵያችን እኛን ለመሆን ለሚሹ ምሳሌ አድርገን ልንገነባት ያስፈልጋል። ቱሪስቶች ስለ ኢትዮጵያ ሲያስቡ በሩቁ የሚመለከቷት ሳይሆን ደግመው ደጋግመው የሚመላለሱባት፣ ተናፋቂ ሀገር እንደሆነች የሚያስቧት አድርገን መገንባት ይጠበቅብናል።

ኢትዮጵያውያኖች የልዩ ውበት፣ የብዝሀነት እና የተፈጥሮ መናገሻ መሆናችንን በዓለም ፊት ለማሳየት የግዴታ የሌለን መፍጠር አይጠበቅብንም። ያለንን ሀብቶች አጉልተን ማሳየት ብቻ በቂ ነው። የመስህብ ችግር ሳይሆን የጎደለንና ያለንን አክብረን፣ በተገቢው መንገድ አጉልተን የማሳየት ችግር ነው ወደ ኋላ እያስቀረን የሚገኘው። ለዚህ ነው እሩቅ ሳንሄድ የመስከረም ወርን ብቻ መዝዘን በትኩረት ብንሰራ የዓለምን ትኩረት መሳብ የሚችል አቅም እንዳለን መረዳት እንችላለን።

በመጨረሻም ኢትዮጵያውያን ከዓመት ዓመት ስንሸጋገር ሁሌም እንደ ትናንቱ ሳይሆን ከትናንቱ የተሻለ ማንነት እየገነባን መሆን እንደሚገባ ለማሳሰብ እወድዳለሁ። ያለን እንዲደበዝዝ ሳይሆን የበለጠ እንዲጎላ፣ አንድነታችን እንዲላላ ሳይሆን፣ ከነበረው እንዲጠነክር፣ ብዝሀ ሀብታችን ትኩረቱ እንዲቀንስ ሳይሆን ይበልጥ በዓለም አደባባይ እንዲታወቅ መሥራት ይገባናል።

እኛን ብለው የሚመጡ እንግዶቻችንን በፍቅር ተቀብለን፣ በኢትዮጵያዊ ባሕል አስተናግደን፣ ባሕል ወጋችንን አስተምረን ደግሞ ለከርሞ ቀጠሮ ይዘው ናፍቀው እንዲመጡ ልንሰራ ይገባል። ይህንን ለማድረግ የሚያስችል አዲስ ሳይሆን ጥንትም የነበረ፤ አብሮን የኖረ ኢትዮጵያውያን ብቻ የምናውቀው እሴት ስላለን እርሱን እንጠቀምበት። ሰላም!!

ስፖርት



የስፖርት ፖሊሲውን ለማሻሻል የተካሄደው ውይይት

ብርሃን ፈይሳ

በየትኛውም ሀገር የስፖርት ዘርፍ ልማት ውስጥ ጠንካራ የስፖርት ፖሊሲ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። የፖሊሲው መኖር ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እና ያንንም ማስፈጸም የሚያስችል ብቃት ያለው አደረጃጀት መኖሩም የግድ ነው። ለአንድ ምዕተ ዓመት የተቃረበ ዕድሜ ያለው የኢትዮጵያ ዘመናዊ ስፖርት፤ ፖሊሲ ተቀርጾለት በሥራ ላይ ከዋለ 27 ዓመታትን አስቆጥሯል። በእነዚህ ዓመታትም ስፖርቱን በማስፋፋት እንዲሁም ሕዝባዊ መሠረት እንዲኖረው በማድረግ ረገድ ውጤቶችን ማግኘት ተችሏል። ይሁን እንጂ ስፖርቱ ባሉበት ውስብስብ ችግሮች ምክንያት በሚፈለገው የእድገት ደረጃ ላይ ሊገኝ አልቻለም።

የስፖርቱ ባለሙያዎች እንዲሁም በኢትዮጵያ ስፖርት ዙሪያ የተሠሩ ጥናቶችም ለሦስር አስርት ዓመታት በተጠጋው ጊዜ ሀገር አቀፍ ፖሊሲው በትክክል ሊተገበር ባለመቻሉ ሊሻሻል ወይም ሊከለስ እንደሚገባው ያመላክታሉ። ከጥቂት ዓመታት በፊት የተዘጋጀው ሀገራዊ የስፖርት ሪፎርም ጥናትና ፕሮግራምም ይህንኑ ያመላከተ ነበር። ፖሊሲው እጅግ መሠረታዊ የሆኑ የስፖርት ልማት አጀንዳዎችን ቢያቅፍም የተሠሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ እንዲሁም ፖሊሲውን ለማስተዋወቅ የተደረጉ ሙከራዎች ውስን በመሆናቸው አመራሩ፣ አስፈጻሚው አካል እንዲሁም በህዝቡ ዘንድ ያለው ግንዛቤም አነስተኛ ሊሆን ችሏል። ፖሊሲውን ለማስፈጸም የሚያስችል መንግሥታዊና ሕዝባዊ አደረጃጀትም እስከታችኛው እርከን ማዋቀር መቻሉም ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ ነው።

የስፖርት ፖሊሲ ለማሻሻል እና አዲስ ረቂቅ የስፖርት አዋጅን የሚመለከት የባለሙያዎች ውይይት ተካሂዷል፤

ፖሊሲው ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ የዓለምም ሆነ የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ በብዙ መልኩ መቀየሩንም ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው። ስፖርት ከፍተኛ የገቢ ምንጭ በሆነበት በዚህ ዘመን የኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲ፤ የስፖርት ንግድን በዓላማ ደረጃ አለማስቀመጡ ከክፍተቶቹ መካከል ይመደባል። የትኩረት ማዕከሉን በመንግሥታዊና ሕዝባዊ አደረጃጀት ብቻ የወሰነው ይህ ዘርፍ የግል ባለሀብቱን ሚና መዘንጋቱ በእድገቱ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ማድረሱም እየተስተዋለ ነው። ስለሆነም ፖሊሲውን ከዓለም አቀፍና ወቅታዊ ሁኔታዎች አንጻር መሠረታዊ ነጥቦችን በመፈተሽ ማስተካከልና መከለስ አስፈላጊ መሆኑን ሪፎርሙ አስገንዝቧል።

በ2012 ዓ/ም በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት የተዘጋጀው ይህ ሪፎርም ያመላከታቸው የመፍትሄ ሃሳቦች ሳይተገበሩ እስካሁን መቆየታቸው ለስፖርቱ ቤተሰብ ጥያቄ ነው። ከሰሞኑ የተዘጋጀ አንድ መድረክም ለዓመታት ሥራ ላይ የቆየውን የስፖርት ፖሊሲ ለማሻሻል እና አዲስ ረቂቅ የስፖርት አዋጅ የሚመለከት የባለሙያዎች ውይይት ተደርጓል። በመድረኩ ንግግር ያደረጉት የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ሸዊት ሻንካ፤ መንግሥትና የሀገሪቱ ሕዝብ የስፖርት ልማትን በማሳደግ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ ለማግኘት እንዲቻል በሥራ ላይ ያለውን የስፖርት ፖሊሲ እና አዲስ የስፖርት ረቂቅ አዋጅ ዙሪያ ግብዓት ለማሰባስብ የተዘጋጀ መድረክ መሆኑን ጠቁመዋል። ንቁ ዜጋና አሸናፊ ሀገርን ለመገንባት ዘርፉ የሚመራበትን የሕግ ማዕቀፍ በመተግበር፤ ህብረተሰቡን በማሳተፍ ሁለንተናዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ መሰል መድረኮች አስፈላጊ እንደሆኑንም አንስተዋል።

የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት በበኩላቸው፣ «ሀገራችን ስፖርቱን በሚገባ እንዳታለማ በፈተናዎች እየተፈተነች ስለሆነ ከዚህ ችግር በዘላቂነት ለመላቀቅ የስፖርት ፖሊሲና አዋጅ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል» ብለዋል። የውይይቱ ተሳታፊዎች በበኩላቸው በቀረቡት ሰነዶች ላይ መካተት አለባቸው ያሏቸውን ሃሳቦች ያነሱ ሲሆን የስፖርቱን ዘርፍ ለማሳደግ የቀረቡ ሰነዶች በታሰበው ልክ ቢሻሻል እምርታዊ ውጤት እንደሚያመጣ መጠቆማቸውን የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር መረጃ ያሳያል።

የጨረታ ማስታወቂያ
የጨረታ ቁጥር 03/2017

የመልካ ኖኖ ክ/ከተማ ከተማ ገንዘብ ጽ/ቤት ለመዘጋጃ ጽ/ቤት አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ የመኪና ማሽነሪዎች ዶዘር, ኤስክቫቴር፣ ግሬደር፣ ሩሎና ደረቅ ጭነት ሽዋር ትራክ (ቦቱ መኪና) መኪና ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ኪራይ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመከራየት ስለሚፈልግ ህጋዊ ተጫራቾች ከዚህ በታች በተገለፀው የተጫራቾች መመሪያ መሠረት ጨረታውን እንዲካፈሉ ተጋብዘዋል፡፡

ዝርዝር ሁኔታዎች

የጨረታውን ሰነድ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ የሥራ ቀናት ከመልካ ኖኖ ገንዘብ ጽ/ቤት የማይመለስ ብር 500.00 (አምስት ሙቶ ብር) በሲንቄ ባንክ በተከፈተው ሂሣብ ቁጥር 10550315712016 ገቢ በማድረግ ዲፖሲት ስሊፑን/ Deposit slip መልካ ኖኖ ክ/ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ገቢ ደረሰኝ በማስቆረጥ የጨረታ ሰነዱን መልካ ኖኖ ክ/ከተማ ገንዘብ ጽ/ቤት ግዥ፣ ንብረት አስተዳደር ጠቅላላ አገልግሎት የሥራ ሂደት አስተባባሪ ክፍል መግዛት የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

የተጫራቾች ግዴታዎች

1. በዘርፉ ህጋዊ የታደሰ ንግድ ፈቃድ በስማቸው ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉ ለዚሁም ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያላቸው እና ማስረጃውን ማቅረብ የሚችሉ ፡፡
3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢና የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያለው እንዲሁም በፌዴራል ገ/ኢ/ትብብር ሚኒስቴር ወይም ኦሮሚያ ገ/ኢ/ትብብር /ቢሮ ባዘጋጀው የዕቃና አገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገቡ እና ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተመሰከረ CPO (ሲፒኦ) ብቻ 50,000.00 ከጨረታ ሰነዱ ጋር የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡
5. ማሽነሪ ኪራይ ላይ የሚሳተፉ ተጫራቾች በሚያቀርቡት ዋጋ ላይ ነዳጅን፤ የመኪና ቅባት፤ ጥገናውንና የሹፌርና ረዳት አበል እና ሌሎች ተዛማጅ ወጭዎች በተጫራቹ ድርጅት (አከራይ) የሚሸፈን ይሆናል።
6. ተጫራቾች ጨረታውን ካሸነፉ በኋላ ማሽነሪዎችን በራሳችው ወጪ መልካ ኖኖ ክ/ከተማ መስሪያ ቤቱ ባዘጋጀው የልማት ቦታ (ሥራ የሚሠራበት ቦታ) ድረስ ማቅረብ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች በጨረታው ላይ የሚያቀርቡት ማሽነሪ ደረጃውን የጠበቀ ሆኖ የባለቤትነት ማስረጃ ወይም ሊብሬ ወይም ህጋዊ የኪራይ ውል አያይዞ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
8. አሸናፊ የሆነ ተጫራች ውል ሲፈርሙ የውል ማስከበሪያ (ዋስትና 10%) ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
9. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ዋጋ በጨረታ ሰነዱ ላይ በመሙላት በኦርጅናል እና በኮፒ በመለየት በፖስታ በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15ኛው ቀን የመንግስት ሥራ ሰዓት መልክ ኖኖ ክ/ከተማ ገንዘብ ጽ/ቤት ግዥ ንብረት አስተዳደር ና ጠቅላላ አገልግሎት የሥራ ሂደት ባለበት ለዚሁ በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
10. ጨረታው በ16ኛው ቀን ጠዋት 4:00 ተዘግቶ በዕለቱ 4:30 ተጨራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት መልካ ኖኖ ክ/ከተማ ገንዘብ ጽ/ቤት ግቢ ውሰጥ ይከፈታል፡፡
11. ጽ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

የመልካ ኖኖ ክ/ከተማ ገንዘብ ጽ/ቤት

Invitation for Expression of Interest

(Andhode-Agamsa Road Project - Balance works of 6 Km Earth works, Drain works and others)

Kalpataru Projects International Limited (KPIL) invites contractors working in road construction to submit expression of interest for carrying out the balance works comprising of Earth works & Drain works, of Nekempte-Bure Road Project, Lot-2-Andhode - Agamsa Section from Km 86 to Km 173.

Contractors are requested to submit a Letter of Interest, incorporating a statement with all supporting evidence, including but not limited to the following.

Profile with Address, Size, year of incorporation and Turnover, Experience in carrying out similar nature of works, Own Equipment/Resources, Any other relevant information

The works briefly consists of Earth works- 1,50,000 Cum Earth works, Hard Rock Excavation- 30,000 Cum, Crushed Sub-base- 15,000 Cum, Crushed base- 15,000 Cum, Earthen/RR masonry/Concrete drains totalling to 27 Km and other related work.

The detailed scope of works shall be sent to qualified entities. The Expression of Interest may be sent to e-mail ID: addisadmin@imcprojects.com within a week. Contact Number-0921467505

Kalpataru Projects International Limited (KPIL)

የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የቤት 27 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0086984041 የሚታወቀው አሸናፊ ያደሳ ፈይሳ በግብር / ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ የቦሌ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት የእጅ በእጅ/ቫት ያልተሰራበት ከቁጥር 00201 እስከ 00250 ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብተው ወንጀል እንዳይሰራበት እና የጠፋ መሆኑን የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ የቦሌ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

የግብር ከፋይ ስም አሸናፊ ያደሳ ፈይሳ